# ታጠቅ

አለም አቀፍ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር
የቲዎሪ መፅሄት

በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር የተዘጋጀ

**የድል ዋስትና ጊዜው በሚጠይቀው**
**መሰረት ላይ የቆመ**
**የወዳጆች አንድነት ነው**

ክፍል አንድ፡ ሚያዝያ 1964

# መግቢያ

የኢትዮጵያ ተማሪዎች እንቅስቃሴ ከጊዜ ወደጊዜ እያደገ መሄዱ ለማንም ስውር አይደለም::እንቅስቃሴያችን መንግስቱ እንዲሻሻል ምክር ያቀርብ የነበረበት ጊዜ ሩቅ አልነበረም::ከንዱ ሰባት አመታት በፊት 'ለጥገና ለውጥ' ቆሞ ነበር::በጭሩ የኢትዮጵያ ተማሪዎች እንቅስቃሴ "መንግስቱ ይህን ያድርግ" በሚል የ'መዘር' አቋም:"መሬት ላራሹ፣የበሳበቱ ስርአትና ኢምፔሪያሊዝም ይውደሙ..." ወደሚለው አብዮተኛ አላማው የተሸገረው አስር አመታት በማይሞላ ጊዜ ውስጥ ነው::በውነቱ ፈጣንና ታላቅ እርምጃ ነው::

ሆኖም የእድገቱ ጊዜ ይጠር እንጂ ጉዳናው ለስሳብ አልነበረም::በእድገቱ ውስጥ ብዙ እንቅፋቶችን ማለፍ ነበረበት::በየደረጃው በአይነታቸውም ሆነ በመጠናቸው የተለያዩ ችግሮች ነበሩበት::ለምሳሌ

- ቅርንጫፍ ማህበራትን በይበልጥ ማጠንከርና አንድነታቸውን ማጥበቅ፣ስራቸውን በይበልጥ ማቀናበር::
- የአባላትን ፖለቲካዊ ንቃት ከፍ ማድረግና ርእዮተአለማቸውን ማጉልመስ — ማለት ተራማጅ ማድረግ::
- የእንቅስቃሴውን መሰረት ማስፋት — ማለት አባላትን ማብዛት::
- ባንድ ወገን ርእዮተአለማዊ ደረጃን ከፍ ለማድረግ፣በሌላው ወገን አባላትን ለማብዛት በሚጥርበት ጊዜ የሚከተለው ችግር::

እነዚህ ችግሮች ለማህበራት አዲስ ነገር አይደሉም:: በዚሁ አቅጣጫ ወደፊትም ሌሎች ችግሮች እንደሚገጥሙን አይጠረጠርም::ትግሉ ሲያድግ ለጊዜው 'ተሸነፉ' የተባሉት ችግሮች ጭምር በአዲስ መልክ ብቅ ማለታቸው አይቀርም::ስለዚህ ሁሉ ዝግጁ ሆኖ መገኘት ያስፈልጋል::ይህንን ማህበሮቻችን ሁሉ በሚገባ የተገነዘቡት ይመስለናል::

ማህበሮቻችንና አበሉች አዲስ ሆኖ ያገኙት ከሁለት አ
መታት ጀምሮ የተፈጠረውን ውስጣዊ ችግር ነው::ከሁለት አመ
ታት ወዲህ በሆነ በልሆነው ነገር መንታረክ:ውሃ ቀጠን ብሉ
ማማረር:መስያየም በማህበሮቻችን ውስጣዊ ህይወት ውስጥ ከል
ክ በላይ ገንነዋል::ተበራሪ ወረቀቶች በየቦታው ይሰራጫሉ፣
የተማሪዎችና የድርጅታቸው ተግባር እስከመረበት ደርሰዋል፣
የማህበራት አንድነት ሳልቶአል::

አዲሱ ችግራችን ይህ ነው::ከማህበራትና በአባላት አ
ዲስ መፍትሄን ይጠበቃል::ለዚህ ተግባር ዝግጁ ሆኖ ለመገ
ኘት አባላት ሁሉ ሲነሱ በሚችሉት ጥያቄዎች ላይ ማስላሰልና
ለጥና ጥናቶች መልስ መስጠት ይኖርባቸዋል:: 'ችግሩ በየት
መጣ?' 'መነሻው ምንድን ነው?' 'ድንገት ዝብ ያለ ነው ወ
ይስ ከንቅናቄያችን ጋር ተያይዞ ያደገ ነው?' መፍትሄ አለ
ው ወይ?' ... ሊመለሱ ከሚገባቸው ጥያቄዎች ጥቂቶች እነዚ
ህ ናቸው::

የሉንዴ ውስጣዊ ማህበር እነዚህን ጥያቄዎች በመመርከ
ዝ ያደረገውን ስራ ጥናት በዚህ መጽሄት ውስጥ — በአንደኛ
ው ክፍል — እስፍረናል::ጥናቱ የተጠቀሱትን ጥያቄዎች በመ
መለስ ብቻ አልተገታም::ጉዳዩን በሩ አድርጉ በሁሉም አንጻ
ር በመመልከት በተጨማሪ አንደኛ ስለተማሪዎችና ስለድርጅታቸ
ው ጠባይ፣ ሁለተኛ ስለተማሪዎችና ስለድርጅታቸው ተግባር፣
ሶስተኛ ስለአንድነትና ስለአንድነታችን መሰረት ብዙ ትምህር
ቶችን ይዞአል::በዚህ አጭር መግቢያችን ላይ ስለነዚህ እው
ን ነጥቦች ማውሳቱ አስፈላጊ አይመስለንም::ጥናቱ ሁሉንም
በዝርዝር ያቀርባል::አንባቢዎች በጥንቃቄና በእርጋታ ካነበ
ቡት በቂ ትምህርት ያገኙበታል::

ይህ ጥናት ጠቃሚ ትምህርትን በማቅረብ ሀልፍ አዲስ
የውይይት ምእራፍ ከፍቶአል ለማለት እንችላለን::ለመገንበት
በሚነበሰ መንፈስ የሚመ፣ ውይይትንም እንደሚያስከትል ተስፋ
እናደርጋለን::አንባቢያ፣ ተጨማሪ አስተያየታቸውን:ውይይቱን
ህይወት በሚሰጥ መንገድ:በጠምሩበት ጥናቱ ወደተፈለገው ግብ
እንደሚያደርሰን እንጠራጠርም::

ታጠቀ'



## እንቅስቃሴያችንና ጊዜያዊ ችግሮች

### ሀ. መግቢያ

የኢትዮጵያ ተማሪዎች እንቅስቃሴ በዚች በትንሽ እድ
ሜው ውስጥ ልዩ ልዩ የታሪክ ደረጃዎችን አልፎአል::እነዚ
ህን ደረጃዎች ካሁን በፊት ባንዳንዱ የመጽሄቶቻችን እትም
ች ውስጥ አቅርበናቸዋል::አሁን እዚህ ላይ እንደገና በዝ
ርዝር አንመለስባቸውም::ለዋና አርእስታችን መግቢያ ይሆኑ
ን ዘንድ የእንቅስቃሴው አንጓ የመሰሉንን ብቻ ባጭሩ ጠቆ
ስን እናልፋለን::

ኢትዮጵያ ከጥቂት አመታት ጀምሮ እንደቀደመው "በአ
ገራቸው ተረስታና እንሱንም ረስታ" የቀረች አገር አይደለ
ችም::በተለይ ከጠላት ወረራ ወዲህ የሃይለስላሴ መንግስት
ለባእዳን በሯን በሰፊው ከፍቶ ኢምፔሪያሊስቶች ገልጥልጥ
አድርገው እንዲያውቋት አድርጓል::

ከኢምፔሪያሊስቶች ጋር መተዋወቅ ከመጣ ወዲህ አገዛ
ዙ አንደኛ ከኢምፔሪያሊስቶች ጋር "የሚያገባቡት" ትርጁማ
ኖች አስፈለጉት::ሁለተኛ ሳስተዳደሩ ዘመናዊ መልክ መስጠ
ት ገዱ ሆነበት::ሶስተኛ ጠንካራ የሆነ ጠቅላይ አገዛዝን
ለመፍጠር ቢል ባለው ባላባታዊ ስርአት ላይ "የቢሮን ስል
ጣን" ማጠንከር ገዱ ሆነበት::ለነዚህ ሁሉ ተግባሮች "የ
ተማሩ" ሰዎች ማስፈለጋቸውን ማንም አይስተውም::

ከጥንት ጀምሮ በነበረው 'የቄስ ትምህርት' ጎን ዘመናዊ ትምህርት መስጠት የተጀመረው በዚህ ምክንያት ነው::በመጀመሪያው ላይ የትምህርት ቤቶ በር የተከፈተው ለመሳፍንት፡ለመኳንንትና 'ለጠዋ' ልጆች ነበር::በኋላ ግን የቢሮው ስልጣን በየጊዜው እየተስፋፋ መሄድ 'የተማሩ' ሰዎችን በብዛት ስለጠየቀ 'የተራ' ህዝብ ልጆችን ጭምር 'ማስልጠን' ግዴታ ሆነ::ከዚህ የተነሳ ትምህርት ቤቶች በየጠቅላይ ግዛቱ ጭምር በመከፈታቸው የተማሪው አካል የጠቅላላው ህብረተሰባዊ መደቦች ውጤት ሊሆን ቻለ::

ትምህርት ቤቶች በብዙ ቦታዎች ከተከፈቱና 'የተራው' ህዝብ ልጆች ጭምር ዘመናዊ ትምህርትን መቅሰም ከጀመሩ አንድ 25 አመታት ቢያልፉ አይቀርም::ነገር ግን ተማሪዎች ከኖሩ 25 አመት ቢሆንም የተማሪዎች እንቅስቃሴ የ25 አመት እድሜ የለውም::በመጀመሪያው ላይ የተማሪዎች እንቅስቃሴ አልነበረም::በዚያን ጊዜ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ከአካባቢያቸው 'ርቀው' የማስተዋል እድል አልነበራቸውም::እርግጥ አልፎ አልፎ ጥያቄዎችን በህብረት ያቀረቡባቸው ጊዜዎች እንደነበሩ ይታወቃል::ግን እነዚህ ጥያቄዎች ምንም ጊዜ ቢሆን ጠጅ መቅጠኑን (ለመኳንንት ልጅ) ምግቡ መበላሸቱን፡አስተማሪው የማይረባ መሆኑን ... ከማመልከት አልፈው አያውቁም ነበር::

በዚያን ጊዜ በነበረበት ሁኔታ ጥያቄዎቻቸው በአካ



ባቢያቸውና በግል ጥቅማቸው ላይ ብቻ ተወስነው መቅረታቸው ሊያስገርመን አይገባም::በዚያን ጊዜ በጠቅላላ ህብረተሰቡ ውስጥ ከነዚህ የተለዩ ጥያቄዎችን ማቅረብ በፍጹም የተለመደ አልነበረም::በተለይ 'የበላይን' ስልጣን ከጥያቄ ማግባት እንደ 'ሀጢአት' የሚቆጠርበት ዘመን ነበር::ከነዚህ ጥያቄዎች አልፎ ለመሄድ ሁኔታው አይፈቅድላቸውም ነበር::

ማንኛውም ንቅናቄ የሚጠነሰሰው በጠባብ አካባቢው የሚታዩትንና በቅርብ የሚመለከተትን ችግሮችና ጉድለቶች በቁልና ጌሽ በማድረግ ነው::ባንድ ቀን ወይም ባንድ ጊዜ አጠቃላይ ጥያቄዎችን ይዞ የሚነሳ ንቅናቄ የለም:: ንቅናቄ የሚያድገው ችግር ችግርን እየሰበ፡ጥያቄ ጥያቄን እየወለደ፡ትግል ትግልን እያስከተለ ሲሄድና በዚያው ልክ የንቅናቄው ተሳታፊዎች የድሮ ድንበራቸውን አልፈው እንዲጠይቁና እንዲመረመሩ ሲገደዱ ብቻ ነው::በቅድሚያ ነገሮችን አርቆ ለማየትና ችግሮችን አፍታትቶ ለማወቅ የሚችል የለም። "ነቢይ" ወይም በእውኑ የሚያልም ካልሆነ በስተቀር::

የኢትዮጵያ ተማሪዎች እንቅስቃሴ የሚያሳየው ይህንኑ እውነት ነው::ከፍ ብለን እንደጠቀስነው መጀመሪያ ላይ ያቀረባቸው ጥያቄዎች ከአካባቢው አላለፉም::ነገር ግን በኋላ በአንድ በኩል የአገሪቱ ሁኔታ በመጠኑ እየለወጠ ሲሄድ፡ በሌላ በኩል ደግሞ የውጩ አለም ነፋስ በኢትዮጵያ በሰማይ ላይ 'ሽው' ማለት ሲጀምር የተማሪዎች ጥያቄ መልኩን መቀየ

ርና አቋማቸውን መለወጥ ያዘ::

አገርቤት ተማሪዎች በፖለቲካ 'መግባት' የጀመሩት በ
1953ቱ ኩዴታ ጊዜ ነው::በ1953ቱ ኩዴታ ጊዜ የአዲስ
አበባ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች 'አብረው በመሰለፍ' በአዲስ
አበባ ውስጥ ታይቶ የማይታወቅ የፖለቲካ ፕሮፓጋንዳ አደረ
ጉ::ከዚያም ቀጥሎ በየአመቱ በሚከበረው 'የኮሌጅ ቀን'
እንደቀድሞው ተጋባዦችን 'በተለመደው' ቲያትርና ስፖርት
በማስደሰት ፈንታ 'የተቃወሙ' ግጥሞችን ማንበብና ፖለቲካ
ዊ ጽሁፎችን መበተን ጀመሩ::እነዚህ ድርጊቶች ባንድ በኩ
ል የተማሪውን ፖለቲካዊ ንቃት በፍ[illegible]፣በሌላ በኩል
ደግሞ ከመንግስቱ ጋር ያለውን ቅራኔ በይበልጥ አከረሩት።

ለመጀመሪያው ጊዜ በርከት ያሉ ተማሪዎች 'ወደባህር
ማዶ' የተሻገሩት በ1942–50 መካከል ሲሆን በ1944–
52 መካከል በብዙ የአውሮፓ አገሮችና በሰሜን አሜሪካ ማ
ህበራት ተቋቋሙ::ለነዚህ ማህበራት መቋቋም መነሻ የሆነ
ው "አንደኛ የብቸኝነት ስሜትና አብሮ የመገኘት ፍላጎት
ሲሆን ሁለተኛ ደግሞ ለአገር መቆጨት ያስከተለው ስሜት ነ
ው" ይላል 'ትግላችን'.[1]::

ውጭ አገር ያሉት ተማሪዎች በነዚህ ማህበራት ሰብሳ
ቢነት ስለጋራ ጉዳይና ስለሀገር ታሪክ፣ስላለው አስተዳደር፣
ስለባህልና ወግ መወያየትና መነጋገር ጀመሩ::የ1953ቱ
ኩዴታ የተሞከረው በዚህ ጊዜ ነው::በዚህ ኩዴታ ውስጥ የ

1 ቁጥር ለተደረገባቸው በመጽሄት
መጨረሻ ማብራሪያ ይሰጣል::



አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች 'አብሮ መሰለፍ'፣ያሳዩ
ት አርአያና ያበረጡት የፖለቲካ ትምህርት ውጭ አገር ለነ
በሩት ተማሪዎች የሰጠው ፖለቲካዊ ህሊና በቀላሉ የሚገመት
አይደለም::

እስከ 1956–57 ድረስ በሀገር ውስጥም ሆነ በው
ጭ የነበሩት ማህበራት ፍላጎትና ምኞት 'የጥገና ለውጥ'
ነበር::ጥያቄያቸው "መንግስቱ እንዲህ ማድረግ ይገባዋል"
የሚል ምክር ወይም ሂስ ከማቅረብ አልፈው 'መሰረታዊ ለው
ጥን' የሚሹና የመንግስቱን እድሜ የሚመረምሩ አልነበሩም::
ሆኖም 'ለጥገና' የቀረቡት ጥያቄዎች ከመንግስቱና ከድሃሪ ሃ
ይሎች አዳማጭን በማግኘት ፈንታ ቁጭትንና ቁጣን ስላስከተ
ሉ 'የጥገና ዘመን' ረጅም እድሜ ሊኖረው አልቻለም::የመ
ንግስቱ "ጆሮየን ያህያ ጆሮ ያድርገው" ማለትና በኩርፊያ
"ተማሪ ምን አገባው" እያሉ መንቀረጠጥ ከሀገሪቱ ሁኔታ
ጋር ሲጠመር የጊዜውን ተራማጆች ተግባር በጣም አቃለለው።
አብዛኛው ተማሪ በመንግስቱ 'መልካም ፈቃድ' ከመጠራጠሩም
በላይ 'የጥገና ለውጥ' ያገራችን ችግሮች መፍትሄ ለመሆኑ
ማነሱን ብቻ ሳይሆን ባሁኑ ስርአት ውስጥ ከስራ ላይ የመ
ዋል እድሉ የመነመነ መሆኑን በቀላሉ መረዳት ቻለ::ከዚህ
ም የተነሳ በርከት ያሉ ማህበራት በያለበት 'ምርምርና ጥ
ናት' ጀመሩ::

በአገራችን ብዙ የተዛቡ ነገሮች እንዳሉ ማህበራትና

አባሳት ቀደም ብለው አውቀው ነበር፡፡ ነገር ግን የመዘባቱ ቀና መነሾ ወይም መነሾዎች ምን እንደነበረ ወይም እንደ ነበሩ ገና አልተገነዘቡም ነበር፡፡ የጥገና ለውጥ ፍላጐት ሊሰፍን — ለጥቂት ጊዜ ቢሆንም ቶሉ — የቻለው ከዚህ አ ለማወቅ የተነሳ ነው፡፡ 'የጥናት ዘመን' ከተጀመረ በኋላ ገን በአገራችን ኢፍትህ የነገሰው፡ ድህነትና መሃይምነት የ በዙት፡ በሽታ ልቅ የተሰደደውና በሽተኞች የበረከቶት፡ ልማት የተዘባቡና አድገት የተዘጠው ... የመንግስቱ 'በጉፈያ ድ' በመጉደሉ <u>ብቻ</u> ባይሆን ጠቅላላው ስርአተ ማህበር — ኢኮኖሚው፡ ፖለቲካው — በመዘነፉ <u>ጭምር</u> መሆኑ ገልጽ ሆነ፡፡ ባለው ስርአተማህበር ውስጥ ምንም አይነት 'ጠቃሚ' ለውጥ ለማድረግ እንደማይቻል፡ አገዛዙ ለህዝቡ 'እድገት' ምንም አይነት ጉጉት ሊኖረው እንደማይችል ብዙ ማህበራትና አባል መገንዘብ ቻሉ፡፡

'የምርመራና የተቃውሞ ዘመን' መሰረቱን የጣለው በ 1957 ገደማ ነው፡፡ የተማሪዎች ማህበራት 'የጥገና ለውጥ ን' ከንተነት ሙሉ በሙሉ ተረድተው የኢትዮጵያ ችግሮች መ ፍትሄ 'መሰረታዊ ለውጥ' ብቻ መሆኑን የተቀበሉት በዚህ ዘ መን ነው፡፡ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ተማሪዎች በየቦታው ያነሱዋቸ ውና የታገሉላቸው ጥያቄዎች ለዚህ የማያስስቱ ምስክሮች ና ቸው፡፡

ባገር ቤት ያሉት ጓዶቻችን እንደቀደሙው መንግስቱ



ማድረግ የሚገባውን የሚያመለክት የተቃውሞ ገጥም በማንበብ ፈንታ "መሬት ላራሹ"፡ "ድህነት ወንጀል ነወይ?" የሚሉትን የትግል አላማዎች ይዘው ወደ 'ጉዳና' ወጡ፡፡ በውጭ አገር የሚገኙ የተማሪዎች ማህበራት ቀና የህዝብ ጠላቶች የባላባ ቱ ስርአትና ኢምፔሪያሊዝም መሆናቸውን በይፋ አስታውቀው የትግላቸውን ቀስት ወደነዚሁ ጠላቶች አቋሙ፡፡

ይህ ዘመን የከፍተኛ ትግል ዘመን እንደነበረ ከፍ ብለን የጠቀስናቸው 'የትግል አላማዎች' ሊያመለክቱ ይችላ ሉ፡፡ ሆኖም በዚህም ጊዜ አንዳንድ መልስ ያላገኙ መሰረታዊ ጥያቄዎች ነበሩ፡፡ ለምሳሌ ያህል ባላባታዊው ስርአት እንዴ ት ይወድቃል? ማን ሊጥለው ይችላል? በቦታው ምን አይነት ስርአትና መንግስት ሊቋቋሙ ይችላሉ? የተማሪዎች ተግባር ምን መሆን አለበት? የተማሪዎች ማህበራት ትግል እንዴት ሊቀናበር ይችላል? ...የሚሉትና እነዚህን የመሳሰሉ ጥያ ቄዎች ገና አልተመለሱም ነበር፡፡

የነዚህ ጥያቄዎች መልሶች "ፍንጭ" ያገኙት በ1959 አም ሞንታርቭ በተደረገው ስብሰባ ላይ ነው፡፡ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በተደረገው 'የአውቀት ዘመቻ' አርባታ ደገፍ ብዙዎ ች መጠነኛ መልሶች አገኝተዋል፡፡ የህዝቡን እከለኛ ታሪካ ዊ ቦታ ከማወቅ ታልፎ ጠላትና ወገንን ለመለየት ተችሏል፡፡ ተማሪዎች "ከህዝቡ ጋር መሰለፍ" አንዱና ዋናው ተግባራቸው መሆኑን ለመገንዘብ ችለዋል፡፡ የህዝባዊት ኢትዮጵያን መልክ

በመጠኑ ለመብል ተሞክርአል::የተማሪ ማህበራት ትግላቸውን የ
ሚያቀናብርላቸው አጠቃላይ ማህበር — አለም አቀፍ የኢትዮ
ጵያ ተማሪዎች ማህበር— ፈጥረዋል::

መልሶች ገና ሙሉ በሙሉ ልክ ሳይሆኑ ይችላሉ::አሁ
ን ባለንበት የትግል ደረጃ ሁሉም ልክ ሊሆኑ አይችሉም::
ወደፊት እየተሻሻሉ መሄድ ይኖርባቸዋል::ነገር ግን ለመልስ
ች አዝማሚያ ትክክለኛነት ጥርጥር የለውም::መልሶችን እያ
ስፋና እያጠለቀ መሄድና ለአዲስ ጥያቄዎች አዲስ መልሶች
መፈለግ እንጂ የጊዜውን መልሶች አቅጣጫ መቀየር አያስፈል
ገም::

ባጭሩ የተመለከትነው ሀተታ የሚያሳየን የተማሪዎች
እንቅስቃሴ ብዙ አይነት ደረጃዎችን ማለፉን ነው::በየደረ
ጃው በአይነትና በመጠን የተለያዩ ብዙ ትግሎችን አከናውና
ል::ዛሬ የኢትዮጵያ ተማሪዎች እንቅስቃሴ የያዘውን ጸረ
ባላባትና ጸረኢምፔሪያሊስት የሆነ አብዮታዊ አቋም ያስገኙ
ት እነዚህ በየደረጃው የተደረጉ ትግሎችና ባስከተሉዋቸው
ጥያቄዎች አነሳሽነት የተደረጉት ጥናቶች ናቸው::የጊዜው
አብዮታዊ አቋም የረጅም ጊዜ ትግልና ጥናት ውጤት ነው::

ይህ አብዮታዊ አቋም ከተመሰረተ በቀላሉ ከአምስት
አመት በላይ ቢሆነው በነዚህ አመታት ውስጥ ተማሪዎች በአ
ንድነት ተሰልፈው በመጋዝ የጸረፊውዳልና የጸረኢምፔሪያሊስት
አቋማቸውን በአንድነት ጠብቀው ለመኖር ችለዋል::ይህ አን



ድነት በሚጠበቅበት ጊዜ ግን በተማሪዎች መሀከል ልዩ ልዩ
አስተያየቶች አልነበሩም ማለት አይደለም::ነበሩ::የጋለ
ትግል ያደረጉበት ጊዜም ነበር::እንዲያውም ከሀሳባቸው
'መሸረር' የተነሱ ከማህበራት የወጡ ወይም የተወገዱ አይ
ጠፉም::

በመሰረቱ ተማሪዎች የሚመነጩት ከጠቅላላው ህብረተሰ
ብዊ አካል ስለሆነ በህብረተሰቡ ውስጥ ያሉ ልዩ ልዩ መደ
ቦች በነሱም መሀከል ይኖራሉ::ከዚህም የተነሳ በተማሪዎች
መሀከል የተለያዩ አስተያየቶች መኖራቸው፡የርእዮተአለም ግ
ጭት መፈጠሩ፡የመደብ ትግል መደረጉ አይቀርም::ስለዚህ በ
ኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበራት ውስጥ የተለያዩ አስተያየቶች
መኖራቸውና አንዳንድ ጊዜም መጋጨታቸው እንግዳ ነገር ሊሆ
ነብን አይገባም::

የልዩ ልዩ አስተያየቶች ግጭት በወግ ከተያዘና ከር
ክሩ በመልክ ከተመራ ትግሉን ሊያሳድጉትና ነፍስ ሊዘሩበት
ከሚችሉት ሃይሎች አንዱ ይሆናል::እዚህ ላይ አንድ ጊዜ ማኦ
ትሴ—ቱንግ ለጓደኞች ያቀረበውን ምክር ብናቀምጥ ጠቃሚ ይ
መስለናል::

> "Oppposition and struggle between ideas of differnt kinds constantly occur within" a group;"this is a reflection within" the group "of contradictions between classes and

between the old and the new in society.If there were no contradictions" in the group "and no ideological stuggles to resolve them,the" group's "life will come to an end."[2]

"All erroneous ideas, all poisonous weeds, all ghosts and monsters, must be subjected to criticism; in no sircumstance should they be allowed to spread unchecked.However, the criticism should be fully reasoned,analytical and convincing, and not rough,bureaucratic,metaphysical or dogmatic."[3]

እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ በኢትዮጵያ ተማሪዎች መሀከል የነበረው 'የሀሳቦች ገጭት' በመልኩና በደንብ በመያዙ ለጠቅላላው እንቅስቃሴ እድገት ከፍተኛ አገልግሎት ሰጥቶአል። የኢትዮጵያ ተማሪዎች እንቅስቃሴ ያደገው ከጠላት ጋር ቢታገል ባገኘው ድል ብቻ አይደለም። በውስጣዊ ህይወቱ ተራማጅና አድሃሪ አስተያየቶች ያደረጉዋቸው ትግሎችም ጎዳናውን አጥርተው የእድገት እርምጃውን እንዳቃለሉት አይጠረጠርም።

ነገ ከሁለት አመታት ወዲህ — በተለይ በዚህ አመት — ስንጠቀምበት የቆየነው የትግል ዘዴ ትንሽ የተዛባ ይመስላል። በዚህ አመት በጸረባሳባትና ጸረኢምፔሪያሊስት አቋማችን ውስጥ በጥሞናና በጓዳዊ መንፈስ መከራከሩ ተረስቶ በሆነ ባልሆነው ሰበብ 'እንደውሽ መናከስ' የክርክር ፈሊ



ጥ ሆናአል። ከክርክሩ ወገየለሽ መሆን የተነሳ አንዳንድ ጊዜ ጸረባሳባትና ጸረኢምፔሪያሊስት አቋማችንን ሌሎች የሁለተኛ ደረጃ ጥያቄዎች ሊሸፍኑት ይደርሳሉ። ይህ መልከቢስ ክርክር ማህበሮቻችንን ከጊዜያዊ ችግር ውስጥ አገብቷቸዋል። የማህበራት አንድነት ጭምር ተዓነዎ በሰሜን አሜሪካ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር በሁለት ወገኖች ተከፍሎአል። የአውሮፓውን ማህበራችንንም ወደዚያው አቅጣጫ ለመፋት የሚዓከፉ ሃይሎች ያሉ ይመስላል።

ለመሆኑ እስከዛሬ ጸንቶ የኖረው የማህበራት 'አንድነት' ዛሬ ለምን ተናጋ? ይህ ሁኔታ የደረሰው በድንገት ነው ወይስ ቀስ በቀስ ያደገ ነው? በጥሞናና በጓዳዊ መንፈስ መከራከር ለምን ተረሳ? ልዩ ልዩ ወገኖች ከየት ብቅ አሉ?

የማህበሮቻችንን ጊዜያዊ ችግሮች ለማቃለል እነዚህንና እነዚህን መሰል ጥያቄዎችን መመርመርና መመለስ ይኖርብናል። በማንኛውም ጊዜ ችግር ከተፈጠረ፡ ችግርን ለማቃለል ከመቻሉ በፊት የግድ የችግሩን ምንጭ ማግኘት አስፈላጊ ነው። እርግጥ ለጊዜው የችግሮቻችንን ምንጮች — መነሾዎች — አፍታትቶ ለማቅረብ እንደሚያዳግት አንስተውም። ጊዜያዊ ችግሮቻችን ገና ለጋዎች ናቸው። ስለዚህም መነሾቻቸውን ለማግኘትና ስራቸውን ጉልጉሉ ለማውጣት ቀላል ነገር አይሆንም። ሆኖም ከፍ ብለን የደረደርናቸውን ጥያቄዎች ለመመለስ ብንሞ

ከር ወደጊዜያዊ ችግሮቻችን መነሾዎች ለመጠጋት እንችላለን
ብለን እንገምታለን።።

ነገር ግን የጥያቄዎችን መልሶች ለማቅረብ ከመቻጣታ
ችን በፊት በቀደሚያ የንቅናቄያችንን ጊዜያዊ ችግሮች ባጭ
ሩ መመልከት አይከፋም።።ዋና ዋናዎችን እንይ።።

## ለ. ጊዜያዊ ችግሮች

ከፍ ብለን ለማሳየት እንደሞከርነው የኢትዮጵያ ተማ
ሪዎች እንቅስቃሴ አስተዳደግ እንደማንኛውም እንቅስቃሴ አ
ስተዳደግ ሁሉ ህገ ተፈጥሮን የተከተለ ነው።።በዚህ የአስተ
ዳደግ እርምጃው ውስጥ ከአንዱ ደረጃ ወደሌላው በተሳለፈ
ቁጥር ከቀደመው በአይነትም ሆነ በመጠን የተለዩ ችግሮች
እየገጠሙት ለእነዚህ የተለያዩ ችግሮች በአይነታቸው ከበፊ
ቱ የተለዩ መፍትሄዎች መስጠት ነበረበት።።በተለይ እንቅስ
ቃሴያችን አብዮታዊ ከሆነበት ጊዜ አንስቶ አዲስና ጥልቅ
ችግሮች ገጥመውት መፍትሄ ለማግኘት ሲጣጣር ብዙ ጉልበትና
ጊዜ ማጥፋቱ ይታወቃል።።ከነዚህ ችግሮች ለአንዳንዶቹ ጊዜ
ያዊ መፍትሄ አገኝቶአል።።አንዳንዶቹ ግና መፍትሄ በመጠባ
በቅ ላይ ናቸው።።

ችግሮቹ የትኞቹ ናቸው?



1 ድርጅታዊ ችግር

ይህ ችግር በአለም አቀፍ ውስጥ የአባላት ማ
ህበረትን ገንኙነት፡የቅርንጫፍ ማህበራትንና
የስራ አስኪያጅ ኮሚቴውን ገንኙነት፡ያወታሳይ
ነት መጠንከርን፡የቅርንጫፍ ማህበራት መጠንከ
ርን ... ይመለከታል።።

2 ፖለቲካዊ ንቃትን የማጉልመስ ጉዳይ

ይህ ደግሞ የጥናት ክበቦችን ማጠንከርን፡ጽሁ
ፍ ማበርከትን፡መጽሄቶች ማስረጨትን፡በፖለቲካ
ሸንጉዎችና በስብሰባዎች ላይ መሳተፍን ...
ይመለከታል።።

3 በውጭ አገር ያሉ ማህበራት መሰረት መጥበብ ችግር

ይህ ችግር በበኩሉ የተሳታፊዎችንና የአባላት
ቁጥርን ማብዛትን፡የደጋፊዎችን ቁጥር መጨመር
ን፡ባይሆን ሲቀር ደግሞወላዋዮችን ጭምር ከስ
ርአቱ ተባባሪነት ማራቅን ... ይመለከታል።።

በጠቅላላ የኢትዮጵያ ተማሪዎች እንቅስቃሴ ፡ከፍ ብ
ለን እንደጠቀስነው፡ባለፉት ሁለት አመታት ከደረደርናቸው
መሰረታዊ ችግሮች በአይነት የተለየ ችግር ገጥሞታል።።ይህ
ችግር የህብረት መንፈስ ማነስን፤የውስጣዊ አንድነት መላ
ላትን ይመለከታል።።እስከዛሬ እንቅስቃሴያችን በህብረት ላ
ይ የተገነባ ጠላትን የመቋቋምና የማጥቃት ችሎታ ነበረው።።

ዘሬ ግን ይህን የህብረት ስራውንናጠላትን የማጥቃት ችሎታ
ውን ይዞ ወደፊት እንዳይራመድ የሚያዳክሙት 'ሁኔታዎች'በ
ውስጡ የተፈጠሩ ይመስላል፡፡መዘለፍና መሰያየም የበዛው፡ ተ
በራሪ ጽሁፎች በየአቅጣጫው የሚበተኑት፡ የድርጅትን አንድነ
ት የሚያሳሉ ድርጊቶች የሚፈጸሙት ከነዚህ ውስጣዊ 'ሁኔታ
ዎች'መፈጠር የተነሳ ነው፡፡

እነዚህ ድርጊቶች የርእዮተአለም ልዩነት ካስከተለው
ትግል ጋር ተያይዘው የመጡ መሆናቸው ገልጽ ነው፡፡እርገጥ
በማህበሮቻችን ውስጥ የርእዮተ አለም ትግል መካሄድ አስፈ
ላጊ ነገር ነው፡፡ይህንን ደጋግመን ተናግረንዋል፡፡ማበልቸ
ት ቢሆንብንም እንደገና እንደገመቀለን፡፡ይህ ትግል ለእን
ቅስቃሴያችን ደህንነትና እርምጃ ዋና መሳሪያ ነው፡፡ይህ
ከቀያቱ አይገባም፡፡ሆኖም ጠቃሚነቱ ቀስትና የሚኖረው ትግ
ሉ በትክክል መንገድ ሲካሄድ ብቻ ነው፡፡ይህን መዘንጋት
ጥቃን ወደጉዳት መለወጥ ይሆናል፡፡የኢትዮጵያ ተማሪዎች
እንቅስቃሴን 'አንድነት' የሚመለከተው ጊዜያዊ ችግር የመ
ጣው የርእዮተአለም ትግል በመካሄዱ አይደለም፡፡ትግሉ የተ
ያዘበት መልክና የተመረበት ዘዴ የተበላሹና የተዛቡ በመሆ
ናቸው ነው፡፡

ለምሳሌ በእንቅስቃሴያችን ውስጥ ለጊዜው ችግራችን
ሰበብ የሆኑ ሶስት የተሳሳተ የርእዮተአለም ትግል ማካሄጃ
መንገዶች ለማመልከት ይቻላል፡፡



1 በክርክር ላይ "የተሳሳተ" አስተያየት ሲሰነዘር
"የተሳሳተውን" አስተያየት በመተንተን ስህተትን
ለማሳየትና "የተሳሳተ" አስተሳሰቦችን ለማረም
በመሞከር ፈንታ በቅድሚያ ሀሳብ አቅራቢውን ለማጥ
ቃትና ለመሰየም መጣር፡፡

2 ጉዳዩ ውይይት በማድረግና በጥሞና በመከራከር "ስ
ህተትን" ተረርሞ በመገባበት ፈንታ 'ወገን' ለይ
ቶ መዘላለፍ፡፡ከዚህም አልፎ ማህበራትን በመከፋፈ
ል 'አንድነትን' ማፍረስ፡፡

3 የኢትዮጵያ ተማሪዎች እንቅስቃሴ የዘረጋቸው የመገ
ናኛ መስመሮች አሉት፡፡በነዚህ መስመሮች በመጠቀም
ፈንታ የግል ወይም የጥቂቶች ሀሳብን በተባራሪ ጽ
ሁፎች ላይ እያሰፈሩ በየፊና በማሰራጨት አለመገባ
ባትን ማስፋፋትና መወናበድን ማስከተል፡፡ለጠላትም
መሳሪያ መሆን፡፡

እነዚህን ሶስት የተሳሳተ የርእዮተአለም ማካሄጃ መ
ንገዶች የጠቀስነው ከናሳችን አፍልቀን አይደለም፡፡በእንቅ
ስቃሴያችን ውስጥ በርግጥ የታዩና የተፈጸሙ ናቸው፡፡ለማስ
ረጃ ያህል እንዳንዶችን ወስደን እንመልከት፡—

1 ባለፈው አመት "The National Question(Re-
gionalism) in Ethiopia" በሚል አርእስት፡

በጥላሁን ታከለ የተዘጋጀ፡አንድ ጽሁፍ ወጥቶ ነበር፡፡በጠቀላላው ጽሁፉ አንዳንድ ጠቃሚ ትምህርቶችን ያቀርባል፡፡የብሄሮችን የራስን እድል በራስ የመወሰን መብት በግልጽ ደገፍ ሀሳቡን በብዙ ታሪካዊ ማስረጃዎች ለመደገፍ ሞክሮአል፡፡ይህን መብት ከኢትዮጵያ ነገዶች ሁኔታ ጋር እያመዛዘነ ለማየት መጠነኛ ጥረት አድርጎአል፡፡ይህ ሁሉ ሙከራ ስሬ ውይይትን ለነፍትና ትምህርትንም ሊሰጥ ይችል እንደነበረ አይጠረጠርም፡፡

ነገር ግን ጽሁፉ በብዙ ቦታዎች ጉልህ የሆኑ የአቀራረብ ጉድለቶችን ይዘአል፡፡ከይዘቱ ጋር ዝምድና የሌላቸው አስተያየቶች በቦደ ቦታዎች ተሰንዝረዋል፡፡በሌላ ቦታና በሌላ ሁኔታ ውስጥ ያገለገሉ የክርክር ዘዴዎችን እንዳሉ ለመገልበጥ የሞከረ ይመስላል፡፡በተማሪ እንቅስቃሴያችን ውስጥ ካዴቶች የሉም፡፡ቢኖሩም ገና አላየናቸውም፡፡ሌኒን "ለካዴቶቹ" የሰጠውን ስያሜ አሁን በተማሪው ንቅናቄ ውስጥ ላሉት ታጋይ ጓዶች "ማስተላለፍ" የሌኒንን "ካዴቶች" ጠባይ አለመረዳት ነው፡፡

ጉድለቱ እነዚህ ብቻ አልነበሩም፡፡ክርክሩ የተቃጣባቸውን አስተያየቶች ባቀረቡት ጓዶች ላይ የማያስፈልጉና አግባብ የሌላቸው፡እንዲያውም አፍራሽ የ



ሆኑ ነቀፌታዎችንና ስያሜዎችን ያዘንባል፡፡ይህ ትክክል አይመስለንም፡፡ለምሳሌ ይህ ጽሁፍ እነዚህን ጓዶች 'ሶሺያል ሾቪኒስትስ' ብሎ ሲሰይም የሰነዘረውን ንኡስ ሀረግ በሚገባ ያሰላሰለበት አይመስልም፡፡'እንዳለ የገለበጠው' ይመስላል፡፡እኛ እንደሚገባን 'ሶሺያል ሾቪኒስት' ማለት በአንደበት ሶሺሊስት በተግባር ትምክህተኛ —አድሃሪ— ማለት ነው፡፡በብሄራዊ ጥያቄ በተሰባሰቡ ጓዶች ላይ እንዲህ ያለውን ዘለፋ መሰንዘር ትክክል ነወይ?

ለማጠቃለል ያህል፡—ጽሁፉ የማስተማር ችሎታ ነበረው፡፡ነገር ግን "በገልበጣ፡በስያሜ" እና በነቀፌታ የተሞላ አቀራረቡ ጠቃሚ ይዘቱን በብዙ ቦታ ስለሸፈነው ትምህርቱ ዋጋውን አጥቶአል፡፡ደራሲው ይዘትና አቀራረብ የተያያዙ ነገሮች መሆናቸውን የሚያጣው አይመስለንም፡፡አቀራረብ ከተበላሸ ይዘቱ መበከሉ አይቀርም፡፡ስለዚህ አፍራሽ ሳይሆን ገንቢ ሂስን ለማቅረብ የሚፈልጉ ሁሉ የግድ አቀራረብንና ይዘትን ማስተካከል ይኖርባቸዋል፡፡

2 አሁንም ባለፈው አመት ሩና በተባለ ጓድ የተደረሰ አንድ ጽሁፍ ወጥቶ ነበር፡፡ይህን ጽሁፍ፡በትግላችን ቁጥር 3፡የካቲት—መጋቢት 1963፡ከመውጣቱ በፊት ደራሲው ራሱ አሰራጭቶታል፡፡ይህ ራሱ አንድ ስህተ

ት ነው፡፡ከዚህም በላይ የጽሁፉን ይዘት የመጻረርና የስያሜ ብዘት ስለበከለው ሊያቀርብ የፈለገው ሀሳብ ተገቢ ቀጋውን አጥቶአል፡፡እርግጥ ይህ ጽሁፍ ከመጽሄት ቦርዱ በቂ መልስ ያገኘ ይመስለናል፡፡ ሆናም ለአንቅስቃሴያችን ጥሎት ያለፈው አርአያ በቀላሉ 'የሚታረም' አይደለም፡፡

3 በተጨማሪ በዚህ አመት "የአንድነት ጥሪ" በሚል አርእስት፡በሆላንድ ውስጣዊ ማህበር ስራ አስኪያጅ ኮሚቴ የተዘጋጀ ጽሁፍ ተሰራጭቶአል፡፡ከመጀመሪያዎቹ ሁለት ጽሁፎች ለየት ያለ መልክ ያለው ጽሁፍ ነው፡፡በአጠቃላይ ስያሜና ንትርክ ከመቃላቱ በላይ አንደኛ ነገር ምንም የማሰጠው ትምህርት የለም፡ሁለተኛ ነገር በማስረጃ የማይደገፉቸውን 'ውንጀላዎች' ያቀርባል፡፡ስያሜ መስጠት፡መሳደብ፡ከዚያም አልፎ በባዶ ቦታ መወንጀል በዚህ ጽሁፍ ውስጥ ልጓማቸውን ለቀቀው ይታያሉ፡፡እንደዚህ ያሉ ድርጊቶች አንቅስቃሴያችን ዘባከቦ ማሳደግ ያለበትን አብዮታዊ ግብረገብነት ከማዳከም አልፎ ሌላ ምንም የሚሰጡት ፍሬ የለም፡፡በተለይ ማስረጃ ያልቀረበለትን ውንጀላ በጠላትም ላይ ቢሆን መሰንዘር ልክ አይደለም፡፡የማያዘልቅ የፕሮፓጋንዳና የማወናበጃ ዘዴ በመሆኑ በአብዮታዊ ትግል ውስጥ ቦታ የለውም፡፡



4 ከፍ ብለው በተጠቀሱት ጎን ሊታይ የሚገባው አንድ ሌላ ጽሁፍ አለ፡፡ Bi-Monthly በሚል ስም በሰሜን አሜሪካኑ ማህበር ስራ አስኪያጅ ኮሚቴ — በከፊል — የወጣ፡፡ይህ ጽሁፍ የማያስፈልጉ ዘለፋዎችን ይዞአል፡፡ጓዶችን "ህጻን" ብሎ መሰየም ከተለመደው 'አባታዊ' ልምድ የወጣ አይመስለንም፡፡በተጨማሪ ጽሁፉ የሚሰጠው ትምህርት በጣም የመነመነ ነው፡፡ከዚህም አልፎ ያለመረጃ ሰዎችን በሚዲያ ላይ በመወንጀል ለጠላት መሳሪያ እስከመሆን ደርሶአል፡፡

እነዚህ ለምሳሌ ያህል የጠቀስናቸው ድርጊቶች ከቀላል ወደከባድ በመሄድ ስያሜን ከማብዛት ተነስተው ለጠላት መሳሪያ እስከመሆን መድረሳቸውን አየን፡፡በያንዳንዱ ጽሁፍ ላይ በቂ ሂስ ለማቅረብ በወደድን ነበር፡፡ግን እዚህ ላይ የተፈለገው የክርክር ዘዴ ያበላሹትን ድርጊቶች ለማመልከት ብቻ ስለሆነ ለጊዜው ሰፊ ሂስ ከማቅረብ መቆጠብን መርጠናል፡፡አለዚያ ከአርእስታችን ብዙ ከመራቃችንም በላይ ጽሁፋችንን ማራዘም ይሆንብናል፡፡

የሆነ ሆኖ ከነዚህ ድርጊቶች የሚገኘውን ትምህርት ባንወስድ አንዳናልፍ ያስፈልጋል፡፡ስህተት ከማመልከት አልፎ አስተያየት የሰነዘሩ ጓዶችን 'ለማጥቃትና' ያለ'ገምት' ቃላትንና ንኡስ ሀረጎችን ለመደርደር መሞከር የሚያስከትለውን 'ጠንቅ' ጓዶች ሁሉ በጥንቃቄ ሊያስላስሉበት ይገባል

ቀደም ብለን እንዳመለከትነው በእንቅስቃሴያችን ውስጥ የርእዮተአለም ትግል መኖሩ ጠቃሚና አስፈላጊ ነገር ነው፡፡ ግን የርእዮተአለም ትግሉ ጠቃሚነት የሚኖረው ትግሉ በትክክል ሲካሄድ ብቻ ነው፡፡ ከፍ ብለን ለምሳሌ የጠቀስናቸውን ድርጊቶች የፈጸሙ ጊዶች "አቀራረባችን ትክክል ነው፣ ማርክሳዊ ሌኒናዊ የሆነ የሂስ አቀራረብ ስልት አለው፣ የተማሪን ትግል ያምታል..." ብለው በመከራከር የድርጊቶቻቸውን ትክክለኛነት ሊያሳምኑን ቢሞክሩ አይቀሩም፡፡ ለማስረጃም ያህል ካለፉ አብዮታዊ የትግል ታሪኮች መሰል ድርጊቶችን ለመጥቀስ ይንጠራሩ ይሆናል፡፡

እርግጥ ነው፦ የአለም የሰራተኛ መደብ ታላላቅ መሪዎች፡ ሌኒንና ማኦ፡ በውስጣዊ የርእዮተአለም ትግል ላይ ሃይለቃልና ስያሜ መስጠትን እንደትግል መሳሪያ ተጠቅመውበታል፡፡ ሆነም ይህን ድርጊታቸውን በአሁኑ ጊዜ — በተለይ በኢትዮጵያ ተማሪዎች እንቅስቃሴ ውስጥ — እንዳለ መውረስ ትክክል አይደለም፡፡ ሌኒንና ማኦ በዚህ ዘዴ ለመጠቀም የተገደዱባቸው ልዩ ልዩ ምክንያቶች ነበሩ፡፡ ሌኒንና ማኦ በዚህ ዘዴ ለመጠቀም የተገደዱት በልዩ ሁኔታ ውስጥ ሆነው ነው፡፡

አንደኛ ነገር የሰራተኛው መደብ ግንባር ቀደም ፓርቲዎች መሪዎች በመሆናቸው የሰራተኛውን መደብ ርእዮተአለም ጥራት በሌሎች መደቦች ርእዮተአለም እንዳይደፈርስ መከላከል ነበረባቸው፡፡ የሰራተኛውን ማንነትና የሰራተኛውን ፓርቲ



ከውጭና ከውስጥ ጠላት መጠበቅ ነበረባቸው፡፡ ትግላቸው በተማሪ ማህበራት ውስጥ አልነበረም፡፡

ሁለተኛ ነገር በዚህ ዘዴ የተጠቀሙት የትግል ደረጃቸው አንድ ከፍተኛ ደረጃ በደረሰበት ወቅት ነው፡፡ በዚህ ዘዴ የተጠቀሙት ፓርቲዎቻቸው ከህዝብ ጋር ተዋህደው የትግል መሪነትን በህዝቡ ዘንድ ባጸደቁበትና ሊከላከሉዋቸው ከመጡ አድሃሪ ሃይሎች ጋር የመረረ ትግል በሚያደርጉበት ጊዜ ነው፡፡ ከዚህም በላይ በትግል የተፈተኑት የፓርቲ 'ካድሮች' አብዮታዊ የሆነ ሂስን ጠቃሚነት በተቀበሉበት ዘመን ነው፡፡

እዚህ ላይ ለማሳሰብ የምንፈልገው የድርጅቶችን አይነት፡ የክርክሮችን አርእስት፡ ክርክሮች የመነጩበትን ቦታና ሁኔታ፡ ክርክሮች የሚካሄዱት በድርጅት ውስጥ ወይስ ከድርጅት ጠላቶች ጋር መሆኑን ሳናመዛዝንና ሳናጣራ የአለም አብዮታዊ መሪዎች የተጠቀሙባቸውን ዘዴዎች እንዳሉ 'ገልብጦ' በኢትዮጵያ ተማሪዎች እንቅስቃሴ ውስጥ መጠቀም፡ መድሃኒት ሲፈልጉ በሽታ ይዞ የመምጣት ያህል መሆኑን ነው፡፡

እስካሁን ለማየት የሞከርነው የርእዮተአለም ትግል ዘዴ መበላሸት የሚያስከትለውን ጉዳት ነው፡፡ ነገር ግን የኢትዮጵያ ተማሪዎች እንቅስቃሴ ጊዜያዊ ችግር በርእዮተአለም ትግሉ በደንብ አለመመራት ብቻ የተፈጠረ አይመስለንም፡፡

ሌሎችም ምክንያቶች አይጠፉም። ለምሳሌ ቀጥሎ የምናቀርበው አንድ ሌላ ምክንያት ነው።

የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበራት የራሳቸው የሆኑ መገናኛ መስመሮች አሉዋቸው። ማንኛውንም አስተያየት ሆነ ሂስ ለመቀበል አጠቃላይ መገናኛዎች ዝግጁ ናቸው። ይህም የአስተያየትና የአስተሳሰብ እንዲሁም የድርጅት አንድነት መሰሪያ ያደርጋቸዋል። ነገር ግን የአንዳንድ ጽሁፎች በሌላ መንገድ በየቦታው መበተን ይህን አገልግሎታቸውን ሊቀንሰው ይችላል። በአጠቃላይ የግንኙነት መስመሮች አለመጠቀም የሚያመጣውን ጉዳት መገመት አዳጋች መሆን አልነበረበትም። የአንቅስቃሴውን ደህንነትና አንድነት ለሚሹ ሁሉ። በቀላሉ እንኳን ሲታሰብ የልዩ ልዩ አስተያየቶችን በየቦታው ስር መስደድ ማስከተሉ፡ የአስተያየቶች ትክክለኛነትና ስህተተኛነት በሁሉም እንዳይመረመር ማገዱ ለማንም መሰት የሚችል ነጥብ አይደለም። ስህተቶችም ሆኑ ጽሁፎች ውሎ በማደር መጠነኛ ተቀባይነት ሊያገኙ ይችላሉ። ከጥቂት ጊዜ በኋላ 'የወገን' መልክ መስጫ መሰረያ የማይሆኑበት ምክንያት የለም። ሌሎችም ተጨማሪ ጉድለቶች አሉት። ጽሁፎችን በአጠቃላይ የመገናኛ መስመሮች አለማስለፍ ራስን ከድርጅት በላይ አድርጎ መቁጠርን ሊያደረጅ ይችላል። ይህም ብቻ አይደለም። አዲስ ድርጅትን እንደመፍጠርም ነው። ከዚህም በላይ አንቅስቃሴውን ለመጉዳት ሆን ብለው ለሚከታተሉ ሰዎች ምቹ ሁኔታ



ን ይፈጥርላቸዋል። ከአጠቃላይ መገናኛ ውጭ ተበትነው ከነበብናቸው አንዳንዶችን ለምሳሌ ያህል እንጥቀስ።

1 "ታህሳሳውያን" በሚል አርእስት የወጣ ጽሁፍ አለ። አርገጥ ጽሁፉ ቦታ የሌላቸው 'ባድ' ቃሎችን ያበዛል። ሂሱ የተደረገበት መጽሄት ከያዘውም የተለየ ትምህርት አያቀርብም። ሆኖም ጽሁፉ በመጽሄቶቻችን ለመውጣት ብቁ ነበር። በውጭ መበተኑ ለምን እንደሁ አልገባንም። ደራሲው በውጭ የበተነው 'የተለየ' ግብና ምክንያት — ትምህርት ከመስጠት ሌላ — ስላለው ይሆንን?

2 "የአንድነት ጥሪ" የሚለውን ቀደም ብለን በይዘቱ ጠቅሰነዋል። ምናልባት በውጭ የተበተነው ብቁ ጽሁፍ አለመሆኑን አቅራቢዎች ተረድተውት ይሆናል።

በንቅናቄያችን ውስጥ 'የአንድነትን' መሳሳትና 'በወገን' የመከፋፈል ስሜትን አስከትለዋል ብለን የምንገምታቸውን ዋና ዋና ሰበቦች አየን። ሌሎችም ሰበቦች ሊኖሩ ይችላሉ። በኛ ግምት ግን ለጊዜው የጎሉት እነዚህ ናቸው።

ችግሮችን ካቀረቡ በኋላ የማቃለያ ዘዴዎችን ማመልከት ያባት ስለሆነ ቀጥሎ መመልከት ያሰብን መፍትሄዎችን ነበር። ነገር ግን ለዚሁ ተግባር ትራስ ሊሆን ስለሚችል በቅድሚያ የችግሮቻችንን መነሾዎች ለማየት እንፈልጋለን። ችግሮቻችን ከየት መጡ? ዋና መነሾዎቻቸው ምንድነው?

## ሐ. የችግሮቻችን መነሾዎች

### አንደኛ፡- የመደቦች መነጠርና 'የወገኖች' መፈጠር

ደጋግመን እንዳመለከትነው የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህ
በራት አባላት የአንድ መደብ ወገን አይደሉም፡፡በኢትዮጵያ
ህብረተሰብ ውስጥ ከሚገኙት መደቦች — ከአብዛኞቹ — የተ
ወጣጡ ናቸው፡፡እርግጥ እያንዳንዱ መደብ በቀጥታ ልክ አይ
ወከልም፡፡ግን የአብዛኛው መደብ ወገኖች በማህበራት አባሎ
ች መሀከል መገኘታቸው አይጠረጠርም፡፡

ልዩ ልዩ መደቦች በአንድነት ቢሰለፉ የየመደባቸውን
ጥቅም ረስተው ሁሉም ለአንድ መደብ ጥቅም ተሰለፉ ማለት
አይደለም፡፡ሁሉም የሚሰለፈው ለየግል መደቡ ጥቅም ነው፡፡
ነገር ግን በአንድ በተወሰነ ጊዜ የአብዛኛው መደብ ጥቅም ሊጣ
ጣም ስለሚችል ሁሉም በአንድነት የመሰለፍ እድል ሊኖራቸው
ይችላል፡፡ልዩ ልዩ መደቦች አብረው የሚሰለፉበት — በግድ
ባይሆን በውድ — ዋና ምክንያት ይህ ብቻ ነው፡፡

እርግጥ ሁሉም መደብ የሚሰለፍለትን አላማ የሚመለከ
ተው ከየመደብ ጥቅሙ አንጻር ነው፡፡ይሁን እንጂ በአንዳን
ዱ ጥያቄዎች ሳይ፡አብረው የተሰለፉ መደቦች፡ተመሳሳይ አስ
ተያየት ሊኖራቸው ይችላል፡፡ነገር ግን ምንም .ጊዜ ቢሆን
በሁሉም ጥያቄዎች ሳይ አንድ አይነት አቋም አይኖራቸውም፡፡
በተስማሙባቸው ነጥቦች ሳይ እንኳን ከጊዜ በኋላ መለያየታ
ቸው አይቀርም፡፡



በአንድ ድርጅት ውስጥ ልዩ ልዩ መደቦች ካሉ የግድ
የመደብ ትግል ይኖራል፡፡በኢትዮጵያ ተማሪዎች እንቅስቃሴ
ውስጥም የዚህ አይነቱ ትግል ቢካሄድ መቆየቱን በመግቢያው
ሳይ የጠቀስነው ታሪክ ያመለክታል፡፡የኢትዮጵያ ተማሪዎች
ሲታገሉ የቆዩት ከውጭ አድሃሪ ሃይሎች ጋር ብቻ አይደለም፡፡
በየትግሉ ደረጃ ልዩ ልዩ አይነት ውስጣዊ ትግልም ሲያደር
ጉ ቆይተዋል፡፡ግን ውስጣዊ ትግላቸው እንደዛሬው ገሉ አን
ድነትን ወደማናጋት የደረሰበት ጊዜ አልነበረም፡፡ዛሬ ግን
እንደምናየው ውስጣዊ ትግሉ ቅጥ አጥቶ የሰሜን አሜሪካኑን
የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር በሁለት 'ወገኖች' ከፍሎታል፡፡
በአውሮፓው ማህበራችንም ውስጥ ብዙዎችን ገራ ሲያጋባ ይታ
ያል፡፡

ለምን?

ይህንን ጥያቄ ለመመለስ ሰፋ ያለ ጥናት ማድረግንና
በርካታ ያሉ ሀቆች መሰብሰብን እንደሚያስፈልግ እንስተውም፡፡
ለጊዜው ያሉንም ጠባጭ ሀቆች የተወሰኑ መሆናቸው ይገባና
ል፡፡ስለዚህ ቀጥለን አስተያየታችንን ስንሰነዝር ለጥያቄው
ሙሉ መልስ እንሰጣለን የሚል እምነት ስላደረብን አይደለም፡፡
የምናቀርበው አስተያየት የጊዜውን ችግር ከትክክለኛው አቅ
ጣጫ እንድንመለከት ይረዳናል በሚል ግምት በመገፋፋትና ከ
ቅን ልቡና የሚፈልቅና በጥሞና የሚመራ ውይይትን እንደሚ
ከፍት ተስፋ በማድረግ ነው፡፡ለአንባቢያቻችን ይህን ካስታ
ወስን ወደጥያቄዎችን እንመለስ፡፡

ኢትዮጵያ በጣም ወደኋላ የቀረች አገር ናት።ይህ ለማንም አንገፃ ነገር አይሆንም።ደጋግመን ተነጋገረንበታል።ወደኋላ የመቅረት ዋና ዋና ምልክቶቿን በየጊዜው ተመልክተናል።የድህነቷ ልክ ማጣት፣ያልተማሩት መብዛት፣የበሽታና የበሽተኞች ስፍር ማጣት ወደኋላ የመቅረቷ ምልክቶች ናቸው።

ይህ ወደኋላ መቅረት በፖለቲካ በኩል ያስከተለውን በድንነትም አያለፍን ሳንነካው አልቀረንም።የፖሊስ ጋጋታ፣የጦር ሰራዊት ጭፍጨፋ፣የባላባትና የኢምፔሪያሊስቶች ገፍ በትከሻው ላይ ተደራርበውበት የሚኖረው የኢትዮጵያ ሰራ ህዝብ በፖለቲካ በኩል ገና ድንገል መሆኑን ጠቃቅሰነው አልፈናል።ግን ይህ የፖለቲካ ድንገልነት ለጠቀሳሳው ትግል የሚሰጠውን ሃይልና ድካም፣በመደብ ትግል ውስጥ የሚጫወተውን ሚና በዝርዝር አልተነጋገርንበትም።በዚህ ጽሁፋችን ውስጥ ጉዳዩን ጠጋ ብለን በመመርመር ከንቅናቄያችን አድገትና ችግሮች ጋር ያለውን ግንኙነት ለመመልከት እንሞክራለን።

በኢትዮጵያችን ለብዙ አመታት ለሰራው ህዝብ የመሰብሰቢያ — በአንድነት የመገናኛ — ሰበቦች የጠበል ማህበር፣እድር፣ዝምድና ... ነበሩ።እርግጥ አንዳንድ ጊዜ በየመንደሩ ሸንጎዎች ይደረጉ እንደነበረ ይታወሳል።የአፍርስታና የዳኝነት ሸንጎዎችም እንደነበሩ አይካደም።ነገር ግን እነዚህ ስበሰባዎች፣—



1ኛ ሰራው ህዝብ በየጊዜው የሚሰበሰብባቸው ቋሚ ሸንጎዎች አልነበሩም።የአንድ ቀበሌ ሰው ችግር ባጋጠመው ቁጥር በባላባቶች ትእዛዝ ለተወሰነ ጊዜ የሚደረጉ ዱለቶች ነበሩ።

2ኛ የቀበሌው ሰዎች በሙሉ መደብ፣ማእርግ ሳይለዩ የሚሰበሰቡባቸው ወይም አገዛዙ ህዝብን የሚቆጣጠርባቸው መሰሪያዎች እንጂ ሰዎች ከግል ጥቅማቸው መሰልነትና ከፖለቲካ አስተያየታቸው መጣጣም የተነሳ በስምምነት የሚደራጁባቸው ወይም የሚገናኙባቸው ሸንጎዎች አልነበሩም።ባጭሩ በኢትዮጵያችን በመደብ ጥቅም ተሳስሮ በአንድነት መሰለፍ የተለመደ አልነበረም።

እዚህ ላይ አንባቢዎች በትክክል እንዲረዱን ያስፈልጋል።መደቦችና የመደብ ትግል አልነበሩም ማለታችን አይደለም።መደቦች ነበሩ።ነባራዊ ሁኔታው ሲያስገድዳቸው መሰል መደቦች ጠቋኘን ለመቋቋም በአንድነት መነሳታቸውንም እንዘነጋም።ነገር ግን የመደብ ትግል ከፍተኛ መገለጫ የሆኑት መደባዊ ህሊናና ፖለቲካዊ ድርጅት እንዳልነበሩ ማመልከታችን ብቻ ነው።

ኢትዮጵያ ለብዙ ጊዜ የፖለቲካ ድንገል ሆና ቆይታለች ለማለት የሚቻለው በዚህ ምክንያት ነው።የፖለቲካ ድርጅት የሚባል ነገር አይታወቅም ነበር።የፖለቲካ ፍች ራሱ ምንን

አንደሚያመለክት የሚያውቁት ሰዎች በጣት ከመቆጠር አያልፉም ነበር::ለብዙዎች ፖለቲካ ማለት የገዥዎች ስራ ነው ወይም ከአስተዳደሩ ውጭ ትርጉም የለውም::እንዲያውም "ፖለቲካ አትገባ" ማለት "ሃይለስላሴን አትቃወም" በሚል የሚተረጎምበት ጊዜ ነበር::

በሙያ ላይ የተመሰረተ ድርጅቶች — የሰራተኞች፣የተማሪዎች፣ያስተማሪዎች — ሳይቀር የተቋቋሙት አሁን በቅርቡ ነው::እነሱም "በፖለቲካ ውስጥ እንዳይገቡ"፣"ከጥቅም ከልሳቸው እንዳይወጡ"፣"በህጉ መሰረት እንዲረመዱ" ዙሪያቸውን በልዩ ልዩ አንቀጾች ታጥረዋል::ራስቸው የተማሪዎች ማህበራት በአከባቢ ነጻነት ስም "በፖለቲካ ነክ" ነገሮች ላይ አስተያየታቸውን ማሰማት ከመጀመራቸው በፊት አቋማቸው ከተለመደው "በአድር መተዳደር፣በዝምድና መተሳሰር" እምብዛም የተለዩ አልነበረም::

ለማጠቃለል ያህል:— በኢትዮጵያችን በመደብና ለመደብ መሰለፍ የተለመደ አልነበረም::የመደቦች ጠብ — 'ከንፍሊክት'— በዝቅተኛ ደረጃ ላይ ይገኝ ነበር::በጠቅላላ ህብረተሰቡ ውስጥ ፖለቲካዊ ህይወት በድን ነበር ለማለት ይቻላል::

ይህ ከጥቂት አመታት በፊት ነበር::አሁን ግን ሁኔታው ለውጦ የጥንቱ ስርአት መናጋት ይዟል::ከተማው በጥያቄዎች ተጨንቋል::ገጠሩ በቁጣ ይተረመሳል::የገበሬዎች



ትንሳኤና ብሄራዊ ንቅናቄዎች በየቦታው መፋፋም ይዘዋል:: የተማሪዎች ትግል ከጊዜ ወደጊዜ እያደገ ሔዶ ዛሬ የአንድ ነተ መነሽ አብሮ መገኘት ሳይሆን እንደሰንሰለት ለማስተሳሰር የሚችል 'ፖለቲካዊ አላማ' ሆኖአል::በውጭ ተጽእኖ የመጣው የአርባታ ሃይል በመጠኑ አድጎ አዲስ ዘዴዎችንና አዲስ መደቦችን ከመፍጠሩም በላይ አዲስ ቅራኔዎችንና አዲስ ጥያቄዎችን አስከትሎአል::

የአርባታ ሃይሎች ማደግና — በተዘባ ሁኔታ ቢሆንም ቅሉ — የትግል መፋፋም በፖለቲካ ህይወት ላይ የሚኖረው ተጽእኖ የሚባት አይደለም::የፖለቲካ እውቀትን ከፍ ያደርጋሉ::የፖለቲካ እውቀት ደግሞ የመደቦች መንጠርን (consolidation)፡ለመደብና በመደብ መሰለፍን ያስከትላል::

የሀብት አያያዝ በተዛነፈበትና የሀብት አደላደል ባልተስተካከለበት አገር ሁሉ የግድ ልዩ ልዩ መደቦች ይኖራሉ::በህብረተሰቡ ውስጥ አዲስ የአርባታ ሃይሎች ሲጸነሱ ደግሞ አዲስ መደቦች መፈጠራቸው አይቀርም::ነገር ግን መደባዊ ንቃት በአንድ ጊዜ የሚመጣ ነገር አይደለም::የመደቦች መንጠርና የመደቦች ትግል የሚመጡት ከብዙ ትግል — ለመደራጀት፣ለመደብ ጥቅም ህጋዊም ሆኑ ህገወጥ ጥያቄዎችን ማቅረብ፣ማነሳሰትና ፕሮፓጋንዳ ማድረግ — በኋላ ነው::የመደቦች ጠብ የተመሰሩ ነባራዊና (objective) ባለቤታዊ (subjective) ሁኔታዎች ከመሟላታቸው በፊት አይመጣም::

ስለዚህ አስተያየት አንድ የስነህብረተሰብ ሊቅ እንዲህ ይላል:—

". . . first a difference of classes, thenclass interest, then class opposition, finally class strife."[4]

ሌኒን ስለዚሁ ነጥብ ያለውን አስተያየት እንስማ:—

". . . class division is ... the ultimate base of ... political grouping; in the final anlysis . . . it always determines that grouping. But this ultimate basis becomes revealed only in the process of historical development."[5]

በያዝነው ወቅት በአገራችን የፖለቲካ ትግል በንቃት የሚካሄደውና በይበልጥ የተስፋፋው በተማሪ መሀከል ነው:: ከሌላው የህብረተሰብ ክፍል ቀደም ብለው የሌላውን አለም ገስጋቤ ለመከታተል መቻላቸውና በአካዳሚ ነጻነት ስም ብዙ የፖለቲካ ትምህርት መቆመበቸው ፖለቲካዊ አውቀታቸውን በቀደሚያ አዳብሮላቸዋል::አብሮ መገኘትና አንዳንዱ የጋራ ተግባሮችን በህብረት መስራት በቀደሚያ ድርጅታዊ ብልሀትን እንዲያገኙና የድርጅትን ጥቅም እንዲገነዘቡ ረድቷቸዋል::



ይህ ሁሉ መግባር በህብረተሰቡ ውስጥ ያሉትን መደቦችና አሰላለፋቸውን ከሁሉ ቀደመው እንዲረዱና በቀደሚያ የመደባቸውን ጥቅም እንዲመለከቱ አድርጓቸዋል::

በጠቅላላው ሲታይ በአንድ ህብረተሰብ ውስጥ ፖለቲካዊ ቡድኖች — የፖለቲካ ቡድን መሰረተ መደብ ነው — በቀደሚያ ብቅ የሚሉትና መደባዊ ጥቅም በቀደሚያ የሚታየው በምሁራን መሀከል ነው::በተለይ ከምሁራኑ ውስጥ ተማሪዎች አዲስ ነገርን ለመቀበል ይበልጥ ዝንባሌ ስላላቸው የፖለቲካ ቡድንም ሆነ የመደብ ጥቅምን መከላከል በቀደሚያና በግልጽ የሚታየው በነሱ ዘንድ ነው::ሌኒን ስለዚህ ጉዳይ እንዲህ ይላል:—

"Students are the most responsive section of the intelligentsia and the intelligentsia are so called because they most resolutely and most accurately reflect and expose the development of political groupings in society as a whole."[6]

ቀደም ብለን እንዳነሳነው በኢትዮጵያ የመደብ ትግል ትክክለኛ መልኩን እየያዘ መሄድ ጀምሮአል::ሰራተኞች በሰራተኛ ማህበር ውስጥ ተደራጅተው ለጥቅማቸው ይታገላሉ::ንኡስ ከበርቴው መብቱን እንደዚሁ በድርጅት አማካኝነት ሲጠ.

ይቀ ይበማል፡፡በየሁኔው የሚደረገው የገበሬዎች ትንቢሊና በመገንፈል ላይ ያሉት ብሄራዊ ንቅናቄዎች የፖለቲካ ድንገልነት ሽፍናት የኖረውን በጥቅምና ለጥቅም መሰለፍ እያጠሩት ቢሄዱ ይታያል፡፡የህዝቡ ትግል ያርበደበዳቸው የገዥ መደቦችም በየመደባቸው መኮልኮል ይዘዋል፡፡

በኢትዮጵያ፡በተለይ ከ1953 ወዲህ፡የተማሪዎች፡የሰራተኞች፡የገበሬዎችና የነገዶች ትግሎች በስፋትም ሆነ በጥልቀት ታይቶ በማይታወቅ አኳኋን ተረመደዋል፡፡1953 እና ተከታዮቹ ጥቂት አመታት በኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን በመላው አፍሪካ የለውጥ ነፋስ የነፈሰባቸው አመታት ነበሩ፡፡በ1952 ጉረቤት አገራችን ሶማሊያ ነጻ ወጣች፡፡1953 እነመንግስቱ ነዋይ የሃይለስላሴን መንግስት ለመገልበጥ የሞከሩበት ዘመን ነበር፡፡1955 የኢትዮጵያ መንግስት ኤርትራን፡የፌደሬሽኑን ውል ጥሶ፡"ጠቅላይ ግዛት" በማድረግ የኤርትራን ህዝብ ያስቆጣበት ጊዜ ነበር፡፡1958 — 1959 ያያቴ የጥጥ ፋብሪካ ሰራተኞች በሳማዊ ሰልፍ ስላደረጉ በፖሊስ ተተኩሰባቸው ሁለት ሰራተኞች የሞቱበት ዘመን ነበር፡፡የኢትዮጵያ ተማሪዎች የኢትዮጵያን ባላባታዊ መንግስት በቀጥታ ከጥያቄ ውስጥ አገብተው "መሬት ላራሹ" ያሉት በ1957 ነበር፡፡በነዚህ አመታት ውስጥ የውጋዴን፡የባሌ፡የሌሎችም ጠቅላይ ግዛቶች ገበሬዎች ተነስተው በመሳሪያ ጭምር አድሃሪውን መንግስት ተቋቁመዋል፡፡



ይህ ሁሉ የመደብ ትግል ለቃሁረት መደባዊ ህሊናን በይበጥ አሳለፈም፡፡ይህ መደባዊ ህሊና በተለይ በተማሪዎች መሀከል በይበልጥ ቢያንጸባርቅ ይታያል፡፡ዛሬ በተማሪዎች መሀከል የሚካሄደውን ትግል መመልከት ያለብን ከዚህ አንጻር ነው፡፡

ከጥቂት አመታት ወዲህ በተማሪዎች መሀከል የተለያዩ 'ወገኖች' መፈጠራቸው ለማንም ግልጽ ነው፡፡ከየቡታው የሚወጡት ልዩ ልዩ ጽሁፎች ለነዚህ ወገኖች መኖር የማያሰስተ ምስክሮች ናቸው፡፡በእኛ ገምት እነዚህ 'ቡድኖች' ወይም 'ወገኖች' በድንገት ከሰማይ ዱብ አላሉም፡፡በጠቅላላው በኢትዮጵያ ውስጥ የሚካሄደው ትግል፡በተለይ ደግሞ የተማሪው እንቅስቃሴ ያፈራቸው ወገኖች ናቸው፡፡የመደብን መንጠር መሰረት አያደረጉ የተነሱ፡መስል አስተያየትና መስል ርእዮተ አለም ያላቸው 'ፖለቲካዊ ቡድኖች' ናቸው ለማለት ይቻላል፡፡

በነዚህ 'ወገኖች' መሀከል ሲካሄድ የምናየው ትንንቅ የመደብ ትግል ነው፡፡አንዳንድ ሰዎች እንደሚገምቱት ትንቅንቅ ከግለሰቦች አለመግባባት የመጣ፡የግለሰቦች ጠብ ያፈለቀው አይደለም፡፡ግለሰቦች በአንዳንድ ጉዳዮች ላይ ብቻ ካለመስማማታቸው የተነሳ የሚያደርጉት ትግል አይደለም፡፡ግለሰቦች በመደባቸውና ለመደባቸው እየተሰለፉ መታገል የመጀመራቸው ምልክት ነው፡፡

የመደቦች መነጠርና የፖለቲካ ቡድኖች መፈጠር በራሱ ምንም አይነት ጉድፍ የለበትም። አንደኛ፡ ለማንኛውም ነገር የሰዎች ፍላጎት ሊገታው ወይም በባዶ ቦታ ሊፈጥረው አይችልም። በማንኛውም ህብረተሰብ ውስጥ ነባራዊ ህግን ተከትሎ የሚመጣ እድገት ነው። ሁለተኛ፡ እንዲያውም የፖለቲካ እድገት መለኪያ ነው። በኛ በተማሪዎች ደረጃ በትክክል ከተመራ ለወደፊት እርምጃችን እንደሚረዳንና የፖለቲካ እርምጃችንን እንደሚያጣርልን አይጠረጠርም።

የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበራት ፖለቲካዊ ከሆኑበት ጊዜ አንስቶ በአንድ በኩል ተራማጅ አስተያየቶችን ለማስፋፋትና ለአባሎቻቸው ፖለቲካዊ እውቀትን ለመስጠት ጥረዋል፤ ለሰፊው ህዝብ መጠነኛ የፖለቲካ ትምህርት ሰጥተዋል። በተለይ ማህበራት "የእውቀት ዘመቻን" ስራችን ብለውና ከፕሮግራማቸው ውስጥ አግብተው መከታተል ከጀመሩ ወዲህ በዚህ በኩል የተደረገው እርምጃ ከፍተኛ ነው ለማለት ይቻላል። በሌላ በኩል ደግሞ የመንግስትን ጥንታዊ አቋም በመጠኑ አናግተዋል። አድሃሪ አስተያየቶችን በብዙ ቦታ አቁስለዋቸዋል። ከንግዲህ ወዲህ የሃይለስላሴ መንግስት "በፈሪሃ እግዚአብሔር" ሰበካውና "በንጉስ አይከሰስ በሰማይ አይታረስ" ተረት ሊገዛ አይችልም።

ቀደም እነዚህን ትግሎች በሚያከናውኑበት ጊዜ ቀናውን ሃይላቸውን የሚፈጁትና

ይበልጡን ጊዜያቸውን



የሚወስደው ከጋራ ጠላታቸው ጋር የሚያደርጉት ትግል ነበር። ሆኖም በመሀከላቸው ደግሞ መጠነኛ ውስጣዊ ትግል ይካሄድ እንደነበረ አይካድም። በየትግሉ ደረጃ መጠነኛና ለጋ የሆነ መደባዊ ትግል አድርገዋል። ግን ምንም ጊዜ ቢሆን የአሁኑ አይነት ውስጣዊ ትግል ገጥሞአቸው አያውቅም።

ቀጥለን በየጊዜው የተደረጉትን መደባዊ ትግሎችና የአሁኑን ትግል አይነተኛ የሚያደርገውን መደባዊ ጠባይ በአጭሩ ለማቅረብ እንሞክራለን።

በቀዳሚያ በተማሪዎች ውስጥ ያሉትን መደቦች ወይም የተቀራረበ ጥቅም ያላቸውን ህብረተሰባዊ ክፍሎች እንስጥ፡-

1ኛ የባላባት መደብ ወገን

2ኛ የከበርቴው መደብ ወገን

3ኛ የንኡስ ከበርቴው ወገን

4ኛ የሰርቶአደሩ ወገን

## የባላባት መደብ ወገን

ጥንት በተማሪዎች ማህበራት ውስጥ "የተገበረበት መሬት እንዴት ይነጠቃል? ሃይማኖት መከበር አለበት፤ ያገር ልማድና ወግ እንዳለ ይጠበቅ፤ የኢትዮጵያ 'አንድነት' በምንም ሁኔታ ሊነካ አይችልም..." እያለ ይከራከር የነበረው ይህ ወገን ነው። እርግጥ የዚህ መደብ አስተያየት

ኢትዮጵያዊ ተማሪዎችን በሙሉ በመጠኑ ሳይገርፍ አልቀረም፡፡ ጣባበውንም ለማዳን ከራሳችን ጋር ገና ብዙ መታገል ይኖርብናል፡፡ የሆነ ሆኖ በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበራት ዘንድ የዚህ መደብ ወገን ተዳክሞአል፡፡ ግን ወደፊት እንደገና ጥያቄዎችን "አዲስ" ይነሳ ይሆናል፡፡ ትግሉ ሲፋፋምና እንጊ ሳይ ሲደርስ ያለው ርዝራዥ እንደገና ለመንጠራራት ሳይሞክር አይቀርም፡፡

## የከበርቴው መደብ ወገን[7]

የዚህ መደብ ወገን ለጊዜው በተማሪ ማህበር ውስጥ አምብዛም ድምጽ የለውም፡፡ ብዙዎቹ ከተማሪ ማህበር ርቀው በውጭ የተማሪን ማህበር ያሰጣሉ፡፡ "የተማሪ ስራ መማር ብቻ ነው፡፡ ባገዛዙ ውስጥ የተማረው ሰው ቀስ በቀስ እየበዛ ሲሄድ አገሪቱ ትሻሻላለች፡፡" የሚል ሀሳብ ከሚወረውሩት አንዳንዶቹ የዚህ መደብ ወገን ናቸው፡፡

በተማሪ ማህበራት ውስጥ ካሉት ጥቂቶቹ የተራማጁን ወገን መርጠዋል፡፡ የመደብ ወይም የወገን ጠባያቸውን ጠብቀው የያዙት ግን ድምጽ ባገኙ ቁጥር ሀሳባቸውን ከመሰንዘር አላቋረጡም፡፡ "ኢትዮጵያ ያለእርዳታ መልማት አትችልም፡፡ አሜሪካኖችን መቃወም አያስፈልግም፡፡ እነሱ ቢወጡ ሶቪየት ህብረት ይተካ የለምይ? ..." እነዚህንና እነዚህን የመሰሉ ሀሳቦች የሚመነጩት ከዚህ ወገን ነው፡፡ ሆኖም በያዝነው ወቅት ከነተ ሀሳባቸው ብዙ አዳማጭ የለውም፡፡



የቢሮው ስልጣን እያደገ ሲሄድ የዚህ መደብ ወገን ቁጥር በተማሪው መሀከል መጨመሩ አይቀርም፡፡ በዚያን ጊዜ ለመንሰራራት ይሞክራል ብሎ መገመት ትክክል ይመስለናል፡፡

## የንኡስከበርቴው ወገን

የከበርቴው ስርአት — ካፒታሊዝም — ባልዳበረባቸውና የተበታተነ የሀብት አያያዝ ባለባቸው አገሮች የዚህ መደብ አባሎች ቁጥር ይበዛል፡፡ በኢትዮጵያም ሁኔታው እንደዚሁ ነው፡፡ በኢትዮጵያ በተለይ 'ተማረ' ከሚባሉት ውስጥ አብዛኞቹ የዚህ መደብ አባሎች ናቸው፡፡

በኢትዮጵያ በዚህ መደብ ውስጥ በአንድ ወገን የሚፈልጉትን የሚያውቁና የአሁኑን አገዛዝ በጥገና ለማከም የሚጥሩ አድሃሪዎች መውጣት ይዘዋል፡፡ በሌላ ወገን ደግሞ እኩልነትን የሚሹና ሶሻሊዝምና የሚመኙ ወጣቶች መውጣት ጀምረዋል፡፡ እርግጥ ከሁለተኛው ክፍል ከድርጊት ይልቅ የአንደበት አብዮታዊነትን የሚያበዙ ይበረክታሉ፡፡ የከበርቴ ዲሞክራሲና የሶሻሊዝም እምነታቸው የተዘበራረቀ ሊሆን ይችላል፡፡ ጨቆሳርእዮተአለማቸው የጸና አይደለም፡፡ ይህ መደብ በተጨማሪ ብዙ 'ግድየለሾችን' አፍርቷል፡፡

ተማሪው ከሞላ ጎደል በሙሉ የዚህ መደብ ወገን ነው ለማለት ይቻላል፡፡ አድሃሪ የሆኑት ከተማሪ ማህበር ርቀው ከከበርቴው ወገን አንዱም ያልራቀ አንዱም ይዘዋል፡፡ ተራማጁ

የሆኑት ግን በተማሪው ማኅበራት ውስጥ ተሰልፈው ለዲሞክራሲና ለደህንነት መቆጋት ይዞቃል::ከመሀከላቸው የባነባተን ስርአት የማይቃወም የለም::አብዛኛው አገረወዳድ ነው::የውጭ ተጽእኖን ይጠላል::ለጊዜው በተማሪው ውስጥ የጸረባላባትና የጸረኢምፔሪያሊስት አቋማችን መሰረት ይህ ክፍል ነው::ብዙዎቹ ሁለተኛም ቀና ቀና ጠላቶች ላይ ነው አውቀው የተገፋው ህዝብ ወገን መሆንን መርጠዋል::

## የሰርቶአደሩ ወገን

በኢትዮጵያ ህብረተሰብ ውስጥ ሰርቶ አደሩ ክፍል ከብዙ መደቦች ይመጣል::የላብአደሩ መደብ አለ::የገበሬው ክፍል አለ::በሁለቱ መሀከል የሚዋልሉት — አሽከር:ገረድ:ሸቃይ:ተላላኪ ወ.ዘ.ተ — ብዙዎች ናቸው::በተማሪው እንቅስቃሴ ውስጥ ለነዚህ ጥቅም የቆመውንና የነዚህን ወገን የመረጠውን ሁሉ በአንድነት የሰርቶአደሩ ወገን ብለንዋል

በቀጥታ ከሰርቶአደሩ ወገን የመጣው ተማሪ ቁጥር በጣም ጥቂት ነው ብለን እንገምታለን::በዚህ በኩል የተደረገ ጥናት ስለሌለ ትክክለኛውን ቁጥር ለመስጠት አይቻልም:: መገመቱ እንኳን ብያዳግት አይቀርም::

የሰርቶአደሩን ወገን ከመረጡት አብዛኞቹ የመጡት ከንኡስከበርቴው መደብ ነው::ከከበርቴውና ከባላባቱ ወገንም የመጡ አይጠፉም::ግን ቁጥራቸው ከዚህ ግባ የሚባል አይመስለንም::



ባለፉት ጥቂት አመታት በተደረገው አብዮታዊ የተማሪዎች ትግል ውስጥ በግንባር ቀደምነት የተሰለፈው ይህ ክፍል ነው::ጸረባላባትና ጸረኢምፔሪያሊስት አላማ የተቀበሉትን ሁሉ ባንድነት አሰልፎ ባንድ በኩል አድሃሪ ሃይሎችንና አድሃሪ ርእዮተአለምን ቢቃጋ:በሌላ በኩል ደግሞ ተራማጅ አስተያየቶችን እያስፋፋ ለራሱም አብዮታዊ እውቀቶችን ቢቀስም ቆይቶአል::ይህ ክፍል በተማሪው እንቅስቃሴ ውስጥ የግራ 'ክንፍ' መሆኑ ነው::

አሁን ባለንበት ወቅት ግን ይህ ለሰርቶአደሩ ጥቅምና ደህንነት የቆመው ክፍል ራሱ በሁለት 'ክንፎች' ተከፍሎአል::ይህ ጊዜያዊ ክፍፍል ነው::ወደፊትም ሌሎች ክንፎች ብቅ ሊሉ ይችላሉ::የሆነ ሆኖ አሁንም ጉዳዩ በሁለት 'ክንፎች' መፈጠር ላይ ብቻ አልቆመም::በነዚህ ሁለት 'ክንፎች' መሀከል 'ቅጥ ያጣ' ትግል መካሄድ ጀምሮአል::በለንበት ወቅት የማህበራችንን 'አንድነት' 'ያላላው' ይህ ቅጥ ያጣ ትግል ነው::ስለትግሉ አይነት:ጥቅምና ጉዳት ቀደም ብለን ተናግረናል::እንደገና ማንሳት አያስፈልግም:: እዚህ ላይ ማመልከት የፈለግነው የጊዜው ችግራችን ዋና መነሾ የዚህ ሁለት ክንፎች መፈጠር ያስከተለው 'ወገየለሽ' ትግል መሆኑን ነው::

የችግራችን — የጊዜው — ዋና መነሾ ይህ ነው::ግን ሌሎችም የማይናቁ:የሁለተኛ ደረጃ ምክንያቶች አሉ::በ

አሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ የግራ 'ክንፍ' እንቅስቃሴ ውስጥ ያለውን መከፋፈል በደንብ ለመረዳት ከተፈለገ እነዚህንም ምክንያቶች መጠመር ያስፈልጋል። እንያቸው።

ሁለተኛ፡— የጠቅላላው አለም የግራ 'ክንፎች' ተጽእኖ

ባሁኑ ጊዜ የጠቅላላውን አለም የግራ እንቅስቃሴ — በተለይ በኢምፔሪያሊስት አገሮችና በመጠኑም በተበዝባዡ አለም፡ ከዚህ ውስጥ በተለይ ወደመበሪያ ትግል ያልገባውን — ብንመለከት በብዙ ትናንሽ ክፍሎች ተከፋፍሎ እናገኘዋለን። የርእዮተአለምና የፖለቲካ ሠንዝበር በሰፊው ሰፍኖባቸው ይታያል። ይህ ሁኔታ በተለይ በኢምፔሪያሊስት አገሮች ሳለነው ኢትዮጵያዊ ተማሪዎች እንግዳ ነገር አይደለም። በየጊዜው ጥቃቅን የግራ 'ክንፎች' ሲፈጠሩና ትንሽ ሰይቆዩ ተከፋፍለው እንደገና ሌሎችን ንኡስን ድርጅቶች ሲወልዱ እናያለን። አንዱ ድርጅት ተብዞ ከትንሽ ጊዜ በኋላ 3—4 ይወጣዋል። ነገሩ በዚህ ተወስኖ አይቀርም። እርስ በርሳቸው መተናነቅ ይጀምራሉ።

ለዚህ ሁኔታ ምክንያቱ ሁለት ይመስለናል። አንደኛ፡ የሚፈጠሩት የግራ ክንፎች በመሰረቱ የምሁራንና የተማሪዎች — ማለት የንኡስከበርቴው — እንጂ በሰራተኛው ውስጥ የተደቆሙ፡ የሰራተኛውን መደብ መሰረት ያደረጉ አይደሉም። ከዚህም የተነሳ የሰራተኛውን መደብ አይነተኛ የሚያደርጉትና የሰራተኛው ሀብት የሆኑት ትእግስት፡ ስነስርአትን ማክበርና በህብረት የመስራት ልምድ ይጐድሉዋቸዋል። የሚታዩባቸው የንኡስከበርቴው ግልፍተኛነት፡ ቸኳይነትና አለሁ—አለሁ ባይነት ነው። ሁለተኛ፡ በስልጣን ላይ ያለው የሞኖፖል ከበርቴ መደብ 'በድርጅቶች' ደካማ ነጥቦች በመጠቀም በሰለጠነው የስለላ ፖሊሱና በመከፋፈያ ዘዴው ይበታትናቸዋል። እርስ በርሳቸው እያጋጠ ያኮሳሽቸዋል።

ይህ በጠቅላላው አለም የግራ እንቅስቃሴ ላይ የሚታየው ሁኔታ የኢትዮጵያንም የግራ እንቅስቃሴ አሁን መምታት ጀምሮአል ለማለት ይቻላል። ቀደም ብለን የበለጠ መከፋፈል ሊኖር ይችላል ያልንበት አንዱ ምክንያት ይህ ሲሆን ለሁኔታው መድረስ ጊዜያዊ ማስረጃዎች የሰሜን አሜሪካው ማህበራችን ከሁለት መከፈልና ባለፈው ነሀሴ ወር አጥበርባሪው የ'ቻሌንጅ' ቅጥር መውጣት ናቸው።

ሶስተኛ፡— የኢትዮጵያ ተማሪዎች እንቅስቃሴ ምንም ፖለቲካዊ ድርጅት በሌለበት አገር ሲታገል ያገኘው ድል ያስከተለው ትምክህት

የኢትዮጵያ ተማሪዎች እንቅስቃሴ ምንም አይነት ፖለቲካዊ ድርጅትና ግልጽ የፖለቲካ ትግል በሌለበት አገር ሲታገል አንዳንድ ትላልቅ ድሎችን አግኝቶአል። ከዚህ የተነሳ አንዳንድ ጓዶች በትምክህት በመቀላት አብዮትን የሚያደ

ርን በር ቶአደሩ ህዝብ ራሱ መሆኑን ረስተው የተማሪ፣ እንቅስቃሴ እንደአብዮተ መሪ አድርገው እስከመውሰድ ደርሰዋል፡፡ ለዚህ ልክ ከታህሳሱ እልቂት በፊት የወጣው 'ታገል' የያዘውን ርእሰአንቀጽ፡በየስብሰባው ሳይሆን በግል ውይይት ጊዜ አንዳንድ ጓዶች የሚሰነዝሩዋቸውን አስተያየቶች — ለመሆኑ ምን እንሰራለን? መለፍለፍ ብቻ፤ ለምን የተማሪው ማህበር መሳሪያ አያነሳም? —፡ሌላው ቀርቶ ባዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎችና በኋላም ውጭ አገር በመገኘ ጓዶቻቸው ሲዘመር የነበረውን "ፋኖ ተሰማራ፤ፋኖ ገባ ደን" የሚለውን መዝሙር ማስታወስ ይበቃል፡፡

እዚህ ላይ አስመገባብት እንዲፈጠር አንፈልግም፡፡ ያገርቤት ጓዶቻችን ባሉበት ሁኔታና አካባቢ እስካሁን የወሰዱዋቸውን፡አንዳንዴም በደማቸው ጭምር የከፈሉላቸውን እርምጃዎች ሁሉ ደግፈናል፡፡ወደፊትም እንደግፋለን፡፡ለማመልከት የምንፈልገው የተማሪው እንቅስቃሴ፡የፖለቲ፣ ድርጅትና ትግል በሌለበት አገር፡እነዚያን የመሰሉ ድሎች መቀዳጀቱ አንዳንድ ጓዶችን 'እንዳስገነፈለ' መረዳት እንዳለብን ነው፡፡ ይህንን ካልተረዳን ያሁኑን የግራ ክንፍ ክፍፍል መረዳት ያዳግተናል፡፡

እናጠቃል፡— ባሁኑ ጊዜ የኢትዮጵያ ተማሪዎች የግራ ክንፍ እሁለት 'ወገን' ተከፍሎአል ለማለት ይቻላል፡፡ የክፍፍሉ ዋና ምክንያት በህብረተሰቡ ውስጥ ያለው የመደብ አሰላ



ለፍ እየነጠረና በግልጽ እየታየ መሄዱ ነው፡፡ ተቀሰም የአለም የግራ እንቅስቃሴ መከፋፈልና የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበራት ያገኙዋቸው ድሎች ያስከተሉት ትምክህት በክፍፍሉ ውስጥ የማይናቅ ሚና ተጫውተዋል፡፡ እንግዲህ ለመደምደም ያህል እነዚህ 'ክንፎች' ምን እንደሚፈልጉ እንጠይቅ፡፡

አንዱ ክፍል የሚፈልገው በጥድፊያ ቶሎ ቶሎ እንድንራመድ፡'ድርጅትን' ቶሎ ፈጥረን ደን እንድንገባ፤ውጊያ አድርገን በፍጥነት አብዮቱን እንድንፈጽም ነው፡፡ ይህ 'ክንፍ' ራሱን እንደአብዮቱ 'እንዝርት' ይመለከታል፡፡ እሱ 'ከሰራ' ሁሉም ነገር በፍጥነት እንደሚከናወን ያምናል፡፡ "ምንድነው የምንጠብቀው? ተቀደምን እኮ" ይላል፡፡ የጊዜው ዋናው ጥያቄ 'ቆራጥ' የመሆንና 'በትጋት' የመስራት ጉዳይ ብቻ ይመስለዋል፡፡ ይህ ሁሉ በግልጽ የንኡስከበርቴው ርእዮተአለም ነጸብራቅ ነው፡፡

ሁለተኛው 'ክንፍ' ደግሞ የተማሪዎችን ተግባር በደንብ የተገነዘበ፤የድርጅት መፍጠር ጉዳይ ከተማሪ ማህበራት ተግባር ውጭ መሆኑን የሚያምን፤አብዮት የህዝቡን ተሳታፊነት የሚፈልግ፡ከመቅጽበት የማይመጣና መሰናደንና የትግል ጊዜን የሚጠይቅ መሆኑን የተረዳ ይመስለናል፡፡ ባሁኑ ጊዜ በሁለቱ ክንፎች መሀል ያለው 'ግጭት' በነዚህ ሁለት አቅጣጫዎች በያዙ አስተያየቶች ላይ የተመሰረተ ነው ብለን እንገምታለን፡፡

ችግሮቻችንን አየን። የችግሮቻችንን መነሾዎች ተመለከትን። አንግዲህ የሚቀረን የችግሮቻችንን መፍትሄዎች መመልከት ነው። አሁን ወደዚህኛው ነጥብ እንመለስ።

## መ. መፍትሔ

በቀጥታ ወደመፍትሄው ከመግባታችን በፊት ስለተማሪዎች ጠቅላላ ጠባይና ስለድርጅታቸው በህርይ በመጠኑ ብናወራ አይከፋም።

በማንኛውም ህብረተሰብ ውስጥ በሙያቸው የተመደቡ ብዙ ህብረተሰባዊ ክፍሎች አሉ። ለምሳሌ ገበሬዎች፣ ሰራተኞች፣ ነጋዴዎች....። በዚሁ ረገድ ተማሪዎችም እንደ አንድ ህብረተሰባዊ ክፍል ሊታዩ ይችላሉ። በአንድ ላይ የሰበሰባቸው የሙያ ፍላጎት ነው። ምንጫቸው ግን ጠቅላላው የህብረተሰብ አካል ነው። ስለዚህም ተማሪዎች የዚህ መደብ ወገን ናቸው ወይም ከሙያቸው ጋር ተሳስረው ያልመጡ ሌሎች አጠቃላይ ጠባዮች አሉዋቸው ለማለት አይቻልም።

በመላው አለም — ህዝባዊ ዴሞክራሲ ከሰፈነባቸው አገሮች በስተቀር — ተማሪዎች በአርባታ ተግባር ውስጥ አይካፈሉም። ተግባራቸው ከሞላ ጎደል በትምህርት ገበታ ላይ ተቀምጠ ወይም በ'ላቦራቶር' ገብቶ የህብረተሰብንና የፍጥረትን ህጎች ማጥናት ነው። ከዚህ ሙያቸው አሳቦችን ማብላላትንና ማጠንጠንን ይማራሉ። ይህ ሙያቸው አዲስ አሳቦች



ን የመቀበልንና 'የማፍለቅን' ስልጣኔ ይሰጣቸዋል። ሆኖም በአርባታ ተግባር ውስጥ ካለመሳተፋቸው የተነሳ ሰ'ቴዎሪና' በድርጊት መሀከል ያለውን 'ዲያሌክቲካዊ' ግንኙነት አቀናብሮ ማየት ይሳናቸዋል። ብዙውን ጊዜ ባለቤታዊነት — ሰብጀክቲቪቲ — የሚያሸንፋቸው ከዚህ የተነሳ ነው። ይህ ብቻ አይደለም። ተማሪዎች ባንድነት ቢገኙም ቅሉ ስራቸውን ለየብቻቸው ስለሚያከናውኑ የግለሰብኝነት ስሜት በይበልጥ ያጠቃቸዋል። ከጉልበት ስራ በመራቃቸውና በኑሮ ዘዴያቸው ከሰርቶአደሩ በመለየታቸው የጉልበት ስራን የመናቅና ከሰርቶአደሩ ኑሮ የመሸሽ ጠባይ አለባቸው። በነገራችንላይ፤ እነዚህ ጠባዮች በሙሉ የምሁራኑ መሆናቸውን አንርሳ።

ከዚህም በላይ የተማሪዎችና የምሁራን — በተለይ የከፍተኛው ደረጃ — ምንጭ ከፍተኞች መደቦች በመሆናቸው፣ በትምህርት ቤት የሚገኙትም ትምህርቶች የነዚሁኑ መደቦች አስተያየት ስለሚያስተጋቡ ተማሪዎችና ምሁራን የዚሁ መደብ አስተያየት ቀራኛ ይሆናሉ።

በመጨረሻ የተማሪዎችን ብሩህ ገጽ መጥቀስ ትክክል ይመስለናል። ተማሪዎች ከህብረተሰብ መደቦች ወይም ክፍሎች ውስጥ አዲስና ተራማጅ አሳቦችን በይበልጥና በቀዳሚያ የመቀበል ዝንባሌ አላቸው። ባጭር ጊዜ ውስጥ የሚንቀሳቀሱ ሃይሎች ናቸው። የለውጥ ፍላጎታቸው ከፍተኛ ነው።

መልካም ጠባዮቻቸው እነዚህ ናቸው። የሰርቶአደሩ ወ.

ግን ግን ብሩህ ጎናቸውን ብቻ ሳይሆን ደካማ ነጥቦቻቸውንም ጠንቅቆ ማወቅ ያስፈልገዋል፡፡ባለቤታዊ አስተሳሰባቸውን፡ ግለሰበኝነታቸውን፡ችኩልነታቸውን በደንብ ተረድቶ በትእግስት ማስተማርና ማረም ይኖርበታል፡፡

እስካሁን ለመግለጽ የሞከርነው የተማሪዎችን መንጭና ጠቅላላ የሆኑ የተማሪዎችን አይነተኛ ጠባዮች ነው፡፡አሁን ደግሞ የተማሪዎችን ድርጅት አይነትና የሚኖሩትን ጠባዮች እንመልከት፡፡

የተማሪዎች ድርጅት ምንድነው? ምን አይነት ጠባዮች ይኖሩታል፡፡

በማንኛውም ህብረተሰብ ውስጥ በሙያቸው የተመደቡ ብዙ ህብረተሰባዊ ክፍሎች — እንደገበሬዎች፡ሰራተኞች፡ምሁራን፡ተማሪዎች ... የመሳሰሉ — መኖራቸውን ከፍ ብለን ጠቅሰናል፡፡በነዚህ ልዩ ልዩ ሙያ ስር የሚገኙ ሰዎች በመደብ ጥቅማቸውና ፍላጎታቸው የተለያዩ ናቸው፡፡ሁሉ ገበሬ የአንድ መደብ አባል አይደለም፡፡ምሁራኑ ከልዩ ልዩ መደብ የተውጣጣ መሆኑን ጠቅሰናል፡፡ነጋዴውም ከአንድ መደብ አይመጣም፡፡ሆኖም ሰዎች የመደብ አንድነታቸውንና ልዩነታቸውን ተገንዝበው ለመደብና በመደባቸው እንዳይሰለፉ.የሚያግዱዋቸው ብዙ እንቅፋቶች ስላሉ በቀደምትነት መደራጀትን የሚጀምሩት ከመደብ መሰሎቻቸው ጋር ሳይሆን ከሙያ ባልንጀሮቻቸው ጋር ነው፡፡ለምሳሌ በመደብ ለመሰለፍ ባህል አንዱ እንቅፋት ነው



የኢኮኖሚ እድገት ወደኋላ መቅረት የመደብ ንቃትና በመደብ የመሰለፍ ዋና ጠንቅ ነው፡፡እንዲሁም የሀብትን ምንጭና ሃይልን የያዘው መደብ የሚያደርገው የተዛባ ፕሮፓጋንዳ የመደብን አሰላለፍ ክፉኛ ያዘባቃል፡፡

እርግጥ በዚህ የሙያ ድርጅት አማካኝነት የሚደረገው ትግል የመደብ ትግል ጠባይ አለው፡፡የመደብ ትግልንም ያዳብራል፡፡ነገር ግን የሙያ ድርጅቶች ብዙውን ጊዜ የሚመሰረቱት ሙያንና ከሙያ የሚገኝ ጥቅምን በመተጋገዝ ለማዳበርና ለማሻሻል ከተነሳ ፍላጎት ነው፡፡እነዚህና እነዚህን መሰል ድርጅቶች ህዝባዊ ድርጅቶች (mass organisation) ተብለው ይጠራሉ፡፡ለምሳሌ የዚሁ አይነት ጠባይ ካላቸው ድርጅቶች ውስጥ የሴቶችን፡የሃይማኖትን ... ድርጅቶች ጭምር መጥቀስ ይቻላል፡፡

የተማሪም ድርጅት መታየት ያለበት ከዚሁ አንጻር ነው፡፡ቀደም ብለን እንደጠቀስነው ተማሪዎችን አንድ ላይ ያገናኛቸው የትምህርት ወይም የሙያ ፍላጎት ነው፡፡ይህም ስለሆነ በመጀመሪያው ላይ እንዲደራጁ የሚገፋፋቸው የትምህርትን ሁኔታ ለማሻሻል፡የግል ኑሮአቸውን ለማዳበርና በጠቅላላው የአካባቢ ችግሮቻቸውን ለማሸነፍ ያላቸው ፍላጎት ነው፡፡ይህ አይነቱ የድርጅት ደረጃ በማናቸውም አገር ተማሪዎች ታሪክ ውስጥ የታለፈ ወይም ተደጋግሞ የሚታይ ነው፡፡

እዚህ ላይ ሳንጠቅሰው ማለፍ የማይገባን አንድ ትም.

ነገር አለ።ይኸውም ስለ ተማሪ ሙያ ነው።ከላይ የጠቀስናቸው የገበሬዎች፡የነጋዴዎች፡... ሙያዎች የአርባታ ሙያዎች ናቸው።ቋሚ የሆኑ ሙያዎች ናቸው።የተማሪዎች ሙያ ግን በአርባታ ላይ የተመሰረተ ወይም ከአርባታ ጋር በቀጥታ የተያያዘ ካለመሆኑ የተነሳ ቋሚ የሆነ ሙያ አይደለም።የተወሰነ እድሜ ያለውና በትምህርት ዘመን የተወሰነ ፡ ሃላፊ ሙያ ነው።ተማሪዎች እንደወረዱ ውሀ የሚተላለፉበት ሙያ ነው።

ይህን ሁሉ ስንመለከት የተማሪ ድርጅት የፖለቲካ ፓርቲ አለመሆኑንና የተማሪን ድርጅት ወደፖለቲካ ፓርቲ ለመለወጥ አለመቻሉን ለመግለጽ ብዙ የሚያሻ አይመስለንም።የፖለቲካ ድርጅት ቋሚ ነገር ነው።ቋሚ ቦታን ይጠይቃል።የፖለቲካ ፓርቲ ልዩ ልዩ መደቦች ጥቅሞቻቸውንና ፍላጐታቸውን ለመጠበቂያና ለመከላከያ የሚያቋቁሙት ድርጅት ነው።ዋና ግቡም መንግስታዊ ስልጣንን መያዝ ነው።የተማሪዎች ምንጭ ግን ጠቅላላው ህብረተሰብ በመሆኑ አንድ አይነት ርእዮተ አለም ሊኖራቸው አይችልም።ከዚህም የተነሳ በአንድንት የፖለቲካ ፓርቲ የመመስረት ችሎታቸው የመነመነ ነው።ስልጣንን ለመያዝ በፓርቲ ስር የመሰለፍ ችሎታም ሆነ ፍላጐት አይኖራቸውም።

ግን የተማሪ ድርጅት የፖለቲካ ፓርቲ አገልጋይ ሊሆን ይችላል።በአብዮት ተግባር ውስጥ ህዝቡን በፖለቲካ ለማጐ



ልመስና በሬው ተማሪ ባንድነት ተደራጅቶ አገልግሎትን ለአንድ አብዮታዊ ፓርቲ እንዲሰጥ መጣር አብዮታዊ ግዴታው ነው።የማንኛውም ጊዜ፡የማንኛውም አገር የተማሪዎች ታሪክ እንደሚያሳየው የተማሪ ድርጅት በዚህ አኳኋን ፓርቲዎችን ማገልገል እንጂ ራሱ ፓርቲ ሆኖ ህዝቡን ነጻ የማውጣት ታሪክ፡ባህርይ፡ችሎታ የለውም።

የኢትዮጵያ ተማሪዎች ድርጅት ከሌሎች ተማሪ ድርጅቶች የተለየ ጠባይ አይኖረውም።ደጋግመን እንዳመለከትነው ብዙ መደቦችን ይይዛል።በዚሁ መጠን ተግባሮችም የተመጠኑ ይሆናሉ።እርግጥ ከኢትዮጵያ አይነተኛ ሁኔታ የተነሳ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር ተግባሮች በስፋትም ሆነ በጥልቀት ከፍተኛ ሚዛን ሊኖራቸው ይገባል።በአይነታቸው ግን ከሌሎች ተማሪዎች ማህበራት በምንም ሊለዩ አይችሉም።

ከአርእስታችን ወጣ ያልነው የተማሪዎችን አጠቃላይ ጠባይና የድርጅታቸውን አይነት ባጭሩ ለመግለጽ በማሰብ ነበር።ግን ስንገነዘበው ከዋናው አርእስታችን ራቅን መሰል።መለስ እንበልና ዋናውን አርእስታችንን እንመልከት።

የተነሳነው ለጊዜያዊ ችግራችን መፍትሄ ለማቅረብ ነው።በኛ አስተያየት ጊዜያዊ ችግሮቻችን መፍትሄ ለማግኘት የሚችሉት የሚከተሉትን ነጥቦች በሚገባ ተረድተን በጥንቃቄ ከስራ ላይ ያዋልናቸው እንደሆን ነው።

1ኛ:- የኢትዮጵያ ተማሪዎች የአንቅስቃሴያቸውን "ተግባሮች" በደንብ ማወቅና በሚገባ መገመት አለባቸው:: ይህንን በትክክል አስከልተረዱ ድረስ አንቅስቃሴያቸው በየጊዜው በችግር ውስጥ መነከሩ አይቀርም::

የኢትዮጵያ ተማሪዎች አንቅስቃሴ "ተግባሮች" ምን መሆን እንዳለባቸው ካሁን በፊት ደጋግመን ተመልክተናል:: ሆኖም ለጊዜው ችግሮቻችን መፈጠር ሰበብ ከሆኑት አንዱ የ"ተግባሮቻችን" መሰት ስለሆነ ዋና ዋና ተግባሮቻችንን እንደገና ብንመለከት አይከፋም::

"ተግባሮቻችን ምንድን ናቸው?

ሀ. ትምር ማስተማር

1 የ'ቲወሪ' ጥናት

ለሚመጣው መራራ ትግል ዝግጁ ሆነን መገኘት የምንችለው በ'ቲወሪ' እውቀታችን ታቀን ስንገኝ ብቻ ነው::ለጸረባላባትና ጸረኢምፔሪያሊስት አቋማችን ትርጉምና ነፍስ መስጠትና በተለይም ውሉ እንደጠፋ በትክር የተወሳሰቡትን የኢትዮጵያ ፖለቲካዊና ማህበራዊ ችግሮች አፍታትቶ ማየት የምንችለው የ'ቲወሪ' እውቀት ሲኖረን ብቻ ነው::የተጣራ የ'ቲወሪ' እውቀት ከሌለን በጸረባላባትና ቢጸረኢምፔሪያሊስት አቋማ ላይ የተመሰረተ ሰፊ አንቅስቃሴያችንን ለማ



ጥበብ ወይም ከመሰረቱ ለማናጋት የሚነሱ አቀኬዎችን በንቃት ለመታገል እንደሚያዳግተን መዘንጋት አይገባንም::

በኢትዮጵያ ተማሪዎች አንቅስቃሴ ውስጥ የ'ቲወሪ'ጥናትን በስርአት መከታተል ከተጀመረ ብዙ ጊዜ አላለፈም:: የዚህ ተግባር ታላቅነት በጣም ከፍ ያለ ስለሆነ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበራት ወደፊት በይበልጥ ሊደክሙለት ይገባል::

አሁን ባለንበት ወቅት በኢትዮጵያ ውስጥ የ'ቲወሪ' ጥናት ከዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች አልፎ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ጭምር እንደተስፋፋ ይታወቃል::ጓደቻችን የኢትዮጵያ መንግስት ጭቆናና ቁጥጥር ሳያገዳቸው በዚህ ተግባር መሰማራታቸው ጥቅሙንና ተግባራቸውን ለይተው በማወቃቸው መሆኑ ገልጽ ነው::

በውጭ ያሉት የኢትዮጵያ ተማሪዎች ከኢትዮጵያ ሁኔታ 'አስከልራቀ' ድረስ ለ'ቲወሪ' ጥናት የተመቸ አጋጣሚ አላቸው::ይህንኑ በመገንዘብ የሰሜን አሜሪካኑና የአውሮፓው ማህበራት በዚህ በኩል አጥጋቢ ሙከራ አድርገዋል::አባሎችን በተደራጀ መልክ ያስጠናሉ::ገን አባላቱ በፖለቲካ እውቀታቸው፡በአይዲዮሎጅ ብስለታቸው፡በድርጅት ዘዴ ስልጣኔያቸው በይበልጥና በብዛት ታቀው ይወጡ ዘንድ ለዚህ ተግባር ካሁኑ የበለጠ ጊዜና ኋልበት መስጠት ያስፈልጋል::

እዚህ ላይ አንድ ቁም ነገር ማስታወስ በጣም ጠቃሚ ይመስለናል፡፡ የሚደረገው ጥናት ፍቹና ህይወት ሊኖረው የሚችለው ጥናቱ ከሀገሪቱ ሁኔታ ጋር ሲያያዝና ሲጣመር ብቻ መሆኑ ለአንድ ደቂቃ እንኳን መዘንጋት የለብንም፡፡ አለዚያ ጥናቱ ሁሉ ለፍቶ መና ከመሆኑም በላይ ይህ ነው የማይባል ጉዳትን ሊያስከትል ይችላል፡፡

2 የህዝቡን ኑሮና ፍለጐት አውቆ መልስ ለማስተማር መቻል

ለእንቅስቃሴያችን የህዝቡን ኑሮና ፍላጐት፣ የህዝቡን ድርጊትና ታሪክ ማወቅ ከአቢይ ተግባሮች አንዱ ነው፡፡ እንቅስቃሴያችን የህዝቡን ሃይልና የትግል አነባስ ጠንቅቆ የመረዳትና በደንብ የማስረዳት ሃላፊነት አለበት፡፡

የኢትዮጵያ አርነት በግድ በባላባቱና በኢምፔሪያሊዝም መቃብር ላይ ማለፍ እንዳለበት በሰፊው ማስረዳት ያስፈልጋል፡፡ ይህ ተግባር ትክክለኛ ግቡን ያገኘ ዘንድ እንቅስቃሴያችን የባላባቱን ጭቆናና የኢምፔሪያሊዝምን ብዝበዛ በጥንቃቄ ተረድቶ ለሰፊውም ህዝብ ሆነ ለአባሎች "ለአገሪቱ በሚስማማ" ቋንቋ ለማስረዳት መቻል አለበት፡፡



3 የአለምን ታሪክና ጊዜያዊ ሁኔታ ማወቅ

እንቅስቃሴያችን የአለምን ታሪክ ማጥናት ያስፈልገዋል፡፡ የአለምን ጊዜያዊ ሁኔታ በደንብ መከታተል አለበት፡፡ የተማሪ ድርጅት ትግልና ህዝባዊ ትግል ያላቸውን ግንኙነትና ልዩነት ማወቅ ይገባዋል፡፡

## ሰ. የማጋለጥ ተግባር

በኢትዮጵያ ያለው የተማሪዎች እንቅስቃሴ የሚያደርገው የማጋለጥ ተግባር በመጠኑም ሆነ በስፋቱ አድጓል፡፡ ዛሬ ከዋናው ከተማ አልፎ በየጠቅላይ ግዛቱና በየወረዳው የተማሪ ትግል በመቀጣጠል ላይ ነው፡፡ ተግባራቸው ምን ያህል ከባድና ታላቅ መሆኑን ለመረዳት የሚያርበደብዱት የመሳፍንት መንግስት የሚያወርዳባቸውን ጥቃትና ግፍ መመልከት ይበቃል፡፡ ከህዝቡም የሚያገኘው የሞራልና የሌላም ድጋፍ በየጊዜው እያደገ መሄዱ የሚያመለክተው ማጋለጡ ስራ የፖለቲካ ውጤት መስጠቱን ነው፡፡ ይህ የማጋለጥ ትግል የአገዛዙን አቋም ከማናጋቱም በላይ ለተማሪዎች የፖለቲካ ንቃትና የትግል ልምድ እንደሚሰጥ አይጠረጠርም፡፡ የጠቅላላውንም ህዝብ ፖለቲካዊ እውቀት ከፍ ማድረጉ አይቀርም፡፡

የኢትዮጵያን ህዝብ ትግልና የኢትዮጵያን ህዝብ ሁኔታ ለአለም ህዝብ በማሳወቅ፣ ኢትዮጵያን ጠቅነው የያዙትን.

ዋንዶ ሳቶች — ኢምፔሪያሊዝምንና የባላባትን ስርአት — ከአሁኑ መንግስት አስተዳደር ጋር ማጋለጥ በውጭ አገር ለምንገኘው ተማሪዎች ከዋና ተግባሮቻችን አንዱ ነው።እስከዛሬ ድረስ በዚህ በኩል መጠነኛ ስራ መደረጉ አይካድም።ሆኖም ወደፊት በይበልጥ መከናወን ያለበት ጉዳይ ነው።

## ሐ. ከህዝቡ ጋር መዋሀድ

1 በኢትዮጵያ የባላባትን ስርአትና ኢምፔሪያሊዝምን ደምስሶ ዋሉ በብዝበዛና በጭቆና ፈንታ ህዝባዊ ዴሞክራሲን መመስረት የሚችለው የሰርቶ አደሩ ህዝብ ሃይል ብቻ ነው።ስለዚህም ጸረባላባትና ጸረኢምፔሪያሊስት አላማን የተቀበሉ ሁሉ ዋና ምኞትና ግብ በሰርቶአደሩ ህዝብ ጉን መሰለፍ፣ከሰርቶአደሩ ጋር መዋሀድ፣ሰርቶአደሩን ህዝብ ማገልገል መሆን ይገባዋል።

የኢትዮጵያ ተማሪዎች እንቅስቃሴ "ከህዝቡ ጋር ተዋሀድ" የሚለውን የትግል አላማ ከተግባሮች አንዱ አድርጉ ከወሰደ በርከት ያሉ አመታት አልፈዋል። በቀላሉ አምስት አመታት ያህል ባያልፉ አይቀርም። ግን እስካሁን ድረስ በዚህ አቅጣጫ የተደረገው ስራ በጣም ትንሽ ነው እንላለን። ተማሪዎች ከህዝቡ



ጋር መዋሀድን ሌት ተቀን ሊያስቡበትና በይበልጥ ሊደክሙበት ይገባል ባዮች ነን።ማንኛውም ሰው አብዮታዊነትን የሚያረጋግጠው 'አብዮታዊ ጥሪን' በድርጊት ላይ በማዋል እንጂ አብዮታዊ ጥሪን እንደዳዊት 'በመድገም' አይደለም።በተለይ የተማሪዎች አብዮታዊነት ዋና መለኪያ ከህዝቡ ጋር መዋሀዳቸውና መሰለፋቸው ስለሆነ አባላት ሁሉ፣የአንደበት አብዮታዊ መሆን ካልፈለጉ፣በዚህ በኩል ብዙ ጥረትን ማድረግ ይገባቸዋል።

2 የባላባትን ስርአትና ኢምፔሪያሊዝምን ለመደምሰስ የግድ አንድ ጸረባላባትና ጸረኢምፔሪያሊስት የሆነ የህዝቡ ተራማጅ ድርጅት ያስፈልጋል።እንገባባ። እርግጥ የተማሪው እንቅስቃሴ ጸረባላባትና ጸረኢምፔሪያሊስት ነው።ነገር ግን ደጋግመን እንዳሳሰብነው የተማሪው ድርጅት ምንም ጊዜ ቢሆን የህዝቡን ድርጅት ቦታ መውሰድና ተግባር መፈጸም አይችልም። ስለዚህ የተራማጅ ተማሪ ዋና ተግባሮች አንዱ ከህዝቡ ጋር በመዋሀድ ጉን፣ይህ የሰርቶአደር ህዝብ ድርጅት እንዲቋቋም ማነሳሳት ነው።

3 እንዲሁም በኢትዮጵያ ለዴሞክራሲ፣ለብሄራዊ ነጻነት የሚዋጉትን — ኤርትራ፣አብነአግ... — መደገፍና አላማቸውን ለህዝብ ማሳወቅ።

በአለም ሏብ ኤራዊ ነፃነት፣ለዴሞክራሲና ለእኩልነት የሚዋጉትን — ቢየትናም፣ካምቦዲያ፣አረቦች፣ሳኦስ ...መደገፍ።

2:— <u>የኢትዮጵያ ተራማጅ ተማሪዎች ከጊዜው ችግራቸው ለመውጣትና ወደፊትም ከችግር ለመራቅ በሁለተኛ ደረጃ ጥያቄዎች ላይ መበጣበጥንና 'መነታረክን' ማቆም አለባቸው።</u>

በያዝነው ወቅት በድርጅታችን ውስጥ የሚደረገው ክርክር ከመጠን በላይ ተዛብቶ ይታያል።ይህ "ክንቶ" ልምድ መሸሸል ይገባዋል ብለን እናምናለን።የክርክርን ዘዴ ካለመድን፣የት መቆም እንዳለብትና የት መቀዛቀዝ እንደሚገባው ለይተን ማወቅ ካልቻልን በሌላ አቅጣጫ እንቅስቃሴያችንን ለማዳበር የሚደረገውን ልፋት ሁሉ የወሃ ሙላት እናደርገዋለን።በታላቅ ጥረት የተገነባውን የተማሪዎች ንቅናቄ በቀላሉ ልንበታትነው እንችላለን።

ለመሆኑ የክርክሩ ዘዴ ለምን ተበላሸ?

ማንኛውም ተራማጅ ድርጅት "አላማዎችን" የሚወስነው የአካባቢውን ነባራዊና ባለቤታዊ ሁኔታዎች መነሻ በማድረግ ነው።የአካባቢ ሁኔታ በደንብ ካልታወቀ የ"አላማዎች" መማታት ሊመጣ ይችላል።ተግባሮችን በትክክል ለመለየትና ለ



መደርደር አስቸጋሪ ይሆናል።እንቅስቃሴውንም <u>ወደፊት</u> ለማራመድ ያዳግታል።

ስለዚህ ማንኛውም አብዮታዊ እንቅስቃሴ "አላማዎችን" በትክክል ለመትለምና የእንቅስቃሴውን አርምጃ በትክክል ለማራመድ የሚችለው "የጊዜው ዋና ዋና ጥያቄዎች ምንድን ናቸው? በአንደኛ ደረጃ መመልከት ያለብን የትኛውን ጥያቄ ነው?" ብሎ ከመረመረ በኋላ አርምጃውን ደረጃ በደረጃ፣ጥያቄዎች በመለከተት ቅደም ተከተል መሰረት፣ሲመራ ብቻ ነው።ይህንን መሰረታዊ እውነት ከተቀበልን ዘንድ የእንቅስቃሴያችንን አቅጣጫ የሚያበዩትን አቢይና ንኡስ ወይም አንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ጥያቄዎችን ከማማታትና ከማደበላለቅ መራቅ ይኖርብናል።

የእንቅስቃሴያችን አቢይና ዋና ጥያቄ ጸረባላባትና ጸረኢምፔሪያሊስት አቋም ነው።ይህ አቋም ለእንቅስቃሴያችን የአንደኛ ደረጃ ጥያቄ የሆነበት ምክንያት ሁለቱ የጥፋት ሃይሎች ከመደምሰሳቸው በፊት ሌሎች የህዝብ ጥያቄዎች መፍትሄ ሊያገኙ እንደማይቻሉ በመታወቁ ነው።ለማንኛውም ድርጅት'ሁሉንም ጥያቄዎች እኩል ማየትና ሁሉንም በአንድ ቦታና ባንድ ዘዴ ለመፍታት መሞከር ከባድና አደካሚ ከመሆኑም በላይ በጣም የተሳሳተ የትግል ዘዴ ነው።በእንቅስቃሴያችን ውስጥ ዛሬ የሚታየው 'የርስበርስ ንትርክና' ለማህበሮቻችን አንድነት ጠንቅ እስከመሆን የደረሰው 'መሰየ

ም' የመጣው የጥያቄዎችን ቅደም ተከተል በሚገባ ልብ ባለማለት በሁሉም ጥያቄዎች ላይ አንድ አይነት የክርክር ዘዴ ለመጠቀም ወይም 'ለመገልበጥ' በመሞከሩ ነው::

የአንድ ማህበር ወይም ድርጅት አባሎች በሁለተኛ ደረጃ ጥያቄዎች ላይ በመሀከላቸው የሚያደርጉት ክርክር ከጠላቶቻቸው ጋር ከሚያደርጉት ክርክር በአይነቱም ሆነ በመጠኑ በጣም የተለያየ መሆን አለበት::ወስጣዊ ክርክራችን እንቅስቃሴያችንን ሊያዳክም ወይም ሊያናጋ አይገባውም::እንዲያውም ማንኛውም የሁለተኛ ደረጃ ጥያቄ ለአንደኛው ደረጃ ጥያቄና ለድርጅታዊ አንድነት ቦታ መስጠት አለበት::

3:— የድርጅታችንን አቋም ማወቅ ከችግሮች መፍትሄዎች አንዱ ነው::

የኢትዮጵያ ተማሪዎች ድርጅት የሰፊው ተማሪ ድርጅት ነው::የፖለቲካ ፓርቲ አይደለም::ከብዙ ሕዝባዊ ድርጅቶች አንዱ ነው::ይህ መረሳት የሌለበት ቁም ነገር ነው::በአሁኑ ጊዜ በእንቅስቃሴያችን ውስጥ የሚታዩት 'ንትርኮችና' ድርጅታዊ አንድነት አስከማናጋት የደረሱት ብጥብጦች ከተፈጠሩበት ምክንያቶች አንዱ የዚህ ቁም ነገር መረሳት ይመስለናል::

በአርግጥ የተማሪ ድርጅታችን በብዙ ረገዶች ገንባር



ቀደም ሆናአል::በብዙ ድርጊቶች የፖለቲካ መልክ ይዞአል:: ሆኖም እነዚህ ድርጊቶች ድርጅታችን የፖለቲካ ፓርቲ አለመሆኑን ሊያስረሱን አይገባም::ከሁለት አመታት ወዲህ የተደረገው የርእዮተአለም ትግልና የተፈጠረው አለመግባባት ሲታይ ብዙዎች የተማሪ ድርጅታችንን እንደፖለቲካ ፓርቲ የወሰዱት ይመስላል::ምናልባት እነዚህ ሰዎች የዚህ አይነት አስተሳሰብ እንደሌላቸው "ይምሉ" ይሆናል::ገን ወደዱም ጠሉ፡ አወቁም ሳቱ ድርጊታቸው የሚያሳየው ከፍ ብለን የጠቀስነውን ነው::የተማሪ ድርጅታችንን እንደፖለቲካ ፓርቲ ቆጥረውታል::

በያዝነው ወቅት የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበራት ጠንከር ያሉ ውስጣዊ ስነስርአት አሉዋቸው::በየጊዜው መጠነኛ የማጋለጥና የፖለቲካ ፕሮፓጋንዳ ያደርጋሉ::በቂ የሆነ የፖለቲካ ትግልም ያደርጋሉ::በኢትዮጵያችን ምንም አይነት ፖለቲካዊ ድርጅት አለመኖሩና ዲሞክራሲያዊ ህይወት የተዳፈነ መሆኑ ሲታሰብ በያዙት አቋም ያለባቸው ሃላፊነት ከፍተኛ መሆኑ አይዘነጋም::ሆኖም ይህ "የተለየ" ሃላፊነት እንቅስቃሴያችንን የፖለቲካ ፓርቲ ሊያደርገው አይችልም::አንዳንድ ጓዶች እንደሚያስመስሉትም እንቅስቃሴያችን 'ነጻ አውጭ' ድርጅት የመሆን አቋም የለውም::

የተማሪ እንቅስቃሴያችንን ተግባር በቦታው አቅርበናል::አሁን እዚህ ላይ እንደገና ማቅረቡ አስፈላጊ አይሆ

ነው፡፡በደንብ ለማስታወስ የምንፈልገው "የድርጅታችንን ስም" በትክክል መወዘትን ዘንግተን የማይችለውን በመጪን መሰረተን ከማናጋት እንድንጠነቀቅ ነው፡፡አንቅስቃሴያችን ተገቢ ተግባሮችን በሚገባ ካከናወነ በቂ ነው፡፡

የአንቅስቃሴያችንን ታሪክ ባጭሩ አስስን፡፡ያጋጠሙትን ችግሮችና የችግሮችን መንስዔዎች ተመለከትን፡፡ትክክል መስለው የታዩንን መፍትሔዎች አቀረብን፡፡በተጨማሪ በዚህን ጊዜ ሁሉ ደጋግመን የጠቀስነው አንዱ ዋ ነገር አለ፡፡ይኸውም በሁሉ ጊዜ አንድነታችንን መጠበቅ እንደሚገባን ነው፡፡ሆኖም በባዶ ቦታ ላይ አንድነት ይኖረን አንልም፡፡የአንድነታችን መሰረት ሊኖረው ይገባል፡፡ይህ የአንድነት መሰረት ምን መሆን አለበት? የዚህ ጥያቄ አጭር መልስ ከፍ ብሎ ይገኛል፡፡ነገር ግን በይበልጥ መብራራት የሚገባው ጥያቄ መስሎ ስለታየን ቀጥሎ ጠለቅ አድርገን ልንመረምረው እንሞክራለን፡፡

## ሠ. ያንድነታችን መሰረት ምንድነው?

ከዚህ በላይ እንዳመለከትነው በመሰረቱ የተማሪዎች ማህበር እንደማንኛውም ህዝባዊ ድርጅት ሁሉ በመጀመሪያው ላይ የሚቋቋመውና የሚታገለው የተማሪን መብትና ደህንነት ለማስጠበቅ ነው፡፡በዚህ ረገድ የተማሪ ማህበር ገብራዊ ማህበርን(professional association) ይመስላል፡፡የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበራትም ጥንት እንደዚህ እንደነበሩ ከዚህ በላይ የተጻፈው ታሪካቸው ያሳያል፡፡በኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን በብዙዎች የአለም ክፍሎችም የተማሪ ማህበራት የሚኖሩበትና የሚኖሩለት ዋናው ምክንያት፡የመቋቋሚያ መሰረታቸው የተማሪን መብትና ደህንነት ማስጠበቅ ነበር፡፡



ነገር ግን የተማሪ መብትና ደህንነት ከህብረተሰቡ ጠቅላላ አቋምና እድገት ውጭ ሊታይ እንደማይቻል ማህበራት ከተገነዘቡ ቆይተዋል፡፡በዚህ አይነቱ ያስተሳሰብ ደረጃ ላይ ከተደረሰ የተማሪ ማህበር የግል መብትና ደህንነት ከመከላከል ያልፍና ህብረተሰቡን በሙሉ የሚመለከቱ ጥያቄዎችን — ማለት የፖለቲካ ጥያቄዎችን — ይዞ ይነሳል፡፡ዛሬ ባለንበት ጊዜ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበራት <u>ያንድነት መሰረት</u> ፖለቲካዊ አላማ የሆነው በዚህ ምክንያት ነው፡፡ለመሆኑ ይህ መሰረት ምንድን ነው?

ያንድነታችን መሰረት ለብዙ አመታት ግልጽ ሆኖ ከኖረ በኋላ ዛሬ ትንሽ የተምታታ ይመስላል፡፡በተማሪ እንቅስቃሴ ውስጥ የሀሳብ መምታታት ይታያል፡፡

አንዳንድ ጓዶች እንደሚሉት ከሆነ ማህበሮቻችን የተመሰረቱበት ርእዮተአለም "ማርክሲዝም—ሌኒኒዝም፡የማኦ ትሴቱንግ ሀሳብ" ነው፡፡ይህ ፈጽሞ ስህተት አስተያየት ነው፡፡አንድ የተማሪ ማህበር በዚህ አይነቱ ርእዮተአለማዊ መሰረት ላይ ሊቆም አይችልም፡፡የተማሪዎችን ማህበር በዚህ

አይነቱ መሰረት ላይ "ሳቅ" ብሎ መምከር የተማሪ ማህበር አንዳይኖር የመጣር ያህል ነው። ከባላባቱ ርእዮተአለም አስከጋራተኛ ርእዮተአለም ያላቸው፤ ከልዩ ልዩ መደብ የተውጣጡ፤ ያባልነታቸው ጊዜ በትምህርት አደሚያቸው ብቻ የተወሰነ ተማሪዎች እንዴት በዚህ አይነቱ መሰረት ላይ ቆመው በአንድነት ይሰለፉ ይባላል? እኛ እንደምናምነው "ማርክሲዝም—ሌኒኒዝም፤ማኦ ትሴ—ቱንግ ሀሳብ" ላይ ተመስርቻለሁ የሚል፤ በርሱ አምናለሁ ለማለት የሚችል ድርጅት የፖለቲካ ፓርቲ ብቻ ነው። ያውም የላብአደሩ ግንባር ቀደም ፓርቲ ብቻ ነው። የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበራት የቆሙበት መሰረት ፈጽሞ "ማርክሲዝም—ሌኒኒዝም፤ማኦ ትሴ—ቱንግ ሀሳብ" አይደለም። ለመሆኑ ካባሎች በዚህ አይነት ርእዮተአለም የሚያምነው ስንቱ ነው። አንግባባ፡— ይህን ስንል "ማርክሲዝም—ሌኒኒዝም፤ማኦ ትሴ—ቱንግ ሀሳብ" በእንቅስቃሴያችን ውስጥ አይስፋፋ ማለታችን አይደለም። ጓዶች የሆኑ ሁሉ ይህን አስተያየት ለማስፋፋት መጣር ይኖርባቸዋል። ነገር ግን ይህን በሚያደርጉበት ጊዜ ሀሳቡን በማስፋፋትና ሀሳቡ "የአንድነታችን መሰረት የሁን" ብሎ በመድረቅ መሀከል ያለውን ልዩነት መርሳት የለባቸውም።

ባሁኑ ጊዜ በተማሪ እንቅስቃሴያችን ውስጥ የሚታየው የሀሳብ መምታታት ይህ ብቻ አይደለም። አንዳንድ ጓዶች ደግሞ በየጊዜው ሊነሱ የሚችሉ አንዳንድ ጥያቄዎችን እንደተ



ማሪ ማህበር የአንድነት መሰረት አድርገው ይወስዳሉ። ለምሳሌ የብሄሮችን ጥያቄ፤ የሴቶችን መከፋፈል...። በነዚህ ጓዶች አስተያየት በነዚህና በመሰሎቻቸው ጥያቄዎች ላይ በማህበራት ውስጥ አንድ አይነት አስተያየትና አቋም ካልኖረ የማህበሮች አንድነት ሊኖር አይችልም። ስለዚህ የተማሪ ማህበር አንድነት የግራም ሆነ የቀኝ ንፉስ ሸው ባለ ቁጥር ከጥያቄ ውስጥ ይገባል። ነገር ግን የማህበሮቻችን አንድነት የሚመሰረተውና ወደፊትም ሊቆም የሚችለው ባንድ በተወሰነ የሁለተኛ ደረጃ ጥያቄ ላይ አባሎች ባላቸው ልዩ ልዩ አስተያየት ላይ አይደለም።

አሁንም እንግባባ፡— ይህን ስንል ማህበሮች በነዚህ ጥያቄዎች ላይ አቋም የላቸውም ወይም አቋም መውሰድ የለባቸውም ማለታችን አይደለም። የግድ በነዚህ ጥያቄዎች ላይ አቋም መውሰድ አለባቸው። ነገር ግን ጥያቄዎች የማህበራት ማቆሚያ መሰረቶች ስላልሆኑ አንዳንድ ወይም ከአባላት አነስተኛው ክፍል በነዚህ ጥያቄዎች ላይ ከማህበሩ አቋም፤ ከአብዛኛው አቋም፤ የተለየ አቋም ሊኖረውና ይህንን አቋሙን በማህበሩ ውስጥ፤ የማህበሩን ደንብና ስርአት ጠብቆ፤ ሊከራከርበት ይችላል።

ቀደም ብለን ማህበሮቻችን የቆሙበትን ዋና የአንድነት መሰረት ተናገረናል። መሰረታችን ጸረባላባትነትና ጸረኢምፔሪያሊስትነት ነው። ይህ መሰረት እስከዛሬ ድረስ ገልጾ

ሆኖ ቆይቶ ነበር፡፡አሁን ባለንበት ወቅት ግን ውዥንብር የገባበት መስሎ ይታያል፡፡ስለዚህ የአንድነታችንን መሰረትና ይዘት እንደገና ባጭሩ ማስታወስ ይጠቅማል ብለን እንገምታለ፡፡

ጸረባላባታዊ አቋማችን የፈለቀው በቀጥታ በኢትዮጵያ ካለው የሀብት አያያዝና የጭቆና አገዛዝ ነው፡፡በአገራችን ዋናው የሀብት ምንጭ መሬት ነው፡፡ከጠቅላላው ህዝብ በቀላሉ ከዘጠና በመቶ የሚያገበው በእርሻ ስራ ይተዳደራል፡፡በጣት የሚቆጠሩ ልኡላን፡መሳፍንትና መኳንንት አብዛኛውን መሬት ከስልጣን ጋር አጣምረው ይዘው የህዝቡን ዘጠና በመቶ እየጨቆኑና የህዝቡ ዘጠና በመቶ ጥሮ ግሮ፡ወጥቶ ወርዶ የሚያፈራውን ምርት እየዘረፉ ይኖራሉ፡፡ከዚህ የተነሳ ዛሬ አገራችን ባንድ በኩል 'ሆዳቸው የተነፋ' ጥቂቶች የሚንደላቀቁባትና የሚዘፍኑባት፡በሌላ በኩል በረሀብ፡በበሽታና በመሃይምነት የታበረ ሰፊ ህዝብ የሚጠረምትባት አገር ናት፡፡የአገራችንን ስርአተማህበር ባላባታዊ ስርአት የሚያደርገው ዋናው ምክንያት ይህ ነው፡፡ዋናው የሀብት ምንጭ መሬትና <u>የገባር</u> ጉልበት በሆነበትና አብዛኛው ለጥቂቶ አዝመራውን በ'ህገ' በሚነጠቅበት አገር ስርአቱ ባላባታዊ ነው፡፡

ከዚህ የተነሳ የጸረባላባት አቋም ዋና ይዘት የመሬትና የዲሞክራሲ ጥያቄዎች ይሆናሉ፡፡ነገር ግን ከነዚህ ውስጥ 'የመሬት ጥያቄ' የመጀመሪያውን ደረጃ ይይዛል፡፡እር



ግጥ እነዚህ ሁለት ጥያቄዎች እንደሰንሰለት የተያያዙ ናቸው፡፡"እንቁ ይቀድማል፣ሌላው ይከተላል" በማለትም ብዙ የክርክር ስልት ሊቀርብ ይችላል፡፡ሆኖም ክርክሩን "በቀደሚያ የመጣችው ዶሮ ናት ወይስ እንቁላል ይቀደማል?" ወደሚለው አይነት ንትርክ ሊያዘነብለው ለማይሸ ሰው 'የመሬት ጥያቄ' አቢይነት የሚሰጥ አይመስለንም፡፡የመሬት ጥያቄ መፍትሄ ካላገኘ ዲሞክራሲን ማምጣት ከቶ የማይቻል ነውና፡፡ለዚህ ነው ከብዙ አመታት ጀምሮ የትግላችን ዋና መመሪያ "መሬት ላራሹ" የሚለው የትግል ጥሪ የሆነው፡፡

እዚህ ላይ አለመግባባት እንዲፈጠር አያስፈልግም፡፡ለዲሞክራሲ መታገል አያስፈልግም ማለታችን አይደለም፡፡ያሁኑን የጭቆና አገዛዝ ለመጣልና በቦታው ዲሞክራሲን ለመገንባት መታገል እንደሚገባ በደንብ እንገነዘባለን፡፡ግን እዚህ ላይ ለማመልከት የፈለግነው ዲሞክራሲው በቃል ብቻ ተወስኖ ሳይቀር ህይወት እንዲኖረው ከተፈለገ መሰረቱ የዘጠና በመቶው የኢትዮጵያ ገበሬ "መሬትን ማግኘት" መሆን እንዳለበት ነው፡፡ዲሞክራሲ የሀብት አያያዝ ነጸብራቅ መሆኑን ካስታወስን ደግሞ ጉዳዩ ከዚህ የተለየ መሆን እንደማይችል መገንዘብ አያዳግትም፡፡ስለዚህ ስለጸረባላባታዊ አቋማችን በምናስላስልበት ጊዜ ወይም ከሱ ተነስተን ወደድርጊት በምናመራበት ጊዜ ይህን ቋሚ እውነት ስተን ነፍስ ያለውን አቋማችንን በደንብ እንዳናደርገው ያስፈልጋል፡፡

ለማጠቃለል ያህል፡— የሰፊው ህዝብ መሬትና የጉልበት ፍሬ በጥቂቶች ተነጥቋል። እነዚህ ዘራፊዎች ሙሉ ስልጣንን ጭምር ስለጨበጡ ሰፊው ህዝብ እንዳችም ሰብአዊ ሆነ የፖለቲካ መብት የለውም። አረመኔያዊ በሆነ የባላባት ግፍ ይሰቃያል። ያንደኛ ደረጃ ለሆኑ ሰብአዊ መብቶች እንኳን እንዳይታገል ገዥው ክፍል ቢቻለው በሃይማኖትና በልምድ አይኑን ለመጋረድ ይሞክራል። ይህ ባይሰራ ቢቀር በጥይትና በቦምብ ይደበድባል። ባጭሩ ዛሬ በኢትዮጵያ ሰፍኖ የሚገኘው ባላባታዊ ስርአት ጸረህዝብና ጸረዴሞክራሲ ነው። የሰፊው ህዝብ ዋና ጠላቶች የዚህ ስርአት 'መሪዎች' ናቸው። የነዚህን የጨለማ ሃይሎች መቃወም፡ ፍትህንና እኩልነትን ለሚያመጣ የመሬት ድልድል፡ ለሰብአዊና ለዴሞክራሲ መብቶች መታገል ጸረባላባታዊ ያሰኛል። የጸረባላባታዊ አቋማችን ዋና ይዘት ይህ ነው። ይህን ይዘት የሚቀበሉ ሁሉ ደግሞ ጸረባላባታዊ ናቸው። በጸረባላባት እንቅስቃሴያችን ውስጥ ቦታ ሊኖራቸው ይገባል። ይህ ብቻ አይደለም። እንቅስቃሴያችን የጸረባላባትነትን ዋና ይዘት የተቀበሉንና ይህን አቋም የማይቃወሙን፡ ስለዚህ አቋም ለመማር የሚሹትን ሁሉ ለማሰለፍ መቻል አለበት።

የጸረኢምፔሪያሊስትነታችን ዋና ይዘትስ ምንድን ነው?

ሁላችን እንደምናውቀውና ደጋግመን እንደተነጋገርነው ያለው ባላባታዊ የገዥ ክፍል የግፍ ስልጣኑን ለማጠንከርና



እድሜውን ለማራዘም የቻለው ከባእድ ሃይሎች ጋር በመሻረክና የራሱን ጥቅም ከገሪቷ ጥቅም አብልጦ በመውሰድ አገሪቷን በአጅ አዙር ለነዚህ ሃይሎች በመሸጡ ነው። በዛሬይቱ ኢትዮጵያ ኢኮኖሚውና ፖለቲካው፡ ጠቅላላ አስተዳደሩ፡ ከዚያም የትምህርት ገበታ፡ ፖሊሱና ጦርሰራዊቱብሜሪካኖች መያዛቸውና የአገሪተ ባህል በሸገተ የኢምፔሪያሊስቶች ልምድ በመኮሳሸት ላይ መሆኑን ማንም ያውቃል።

ኢምፔሪያሊስቶች — በተለይ የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም — የተናጋውን የባላባት ስርአት ደገፈው የያዙት ያገሪቷን ሀብትና የሰርቶአደሩን ህዝብ ጉልበት በቀላሉ ለመበዝበዝ ስለሚያስችለው ነው። ኢምፔሪያሊዝም አገሪቱን የሚበዘብዘው የባላባቱን ስርአት መስሳል በማድረግ ነው። ስርአቱ ደግሞ ያለኢምፔሪያሊስቶች ድጋፍ መቆም አይችልም። እነዚህ ሁለት የጨለማ ስርአቶች በጣም የተያያዙና የተደጋገፉ፡ በአሁኑ ጊዜ እንደጥርስና ድድ ሆነው መታየት ያለባቸው ሃይሎች ናቸው። ስለዚህ የኢትዮጵያን የጨለማ ስርአት ለመታገል የተነሳ ሁሉ ኢምፔሪያሊዝምን ባይታገል ሊያልፍ አይችልም። ለዚህ ነው ጸረባላባት የሆነው የኢትዮጵያ ተማሪዎች እንቅስቃሴ የግድ ጸረኢምፔሪያሊስት መሆን ያለበት።

ኢምፔሪያሊዝም አንዱ የኢትዮጵያ ህዝብ ጠላት ነው። የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ አፍኖ ከያዙትና የኢትዮጵያን ህዝብ ማፈናፈኛ አሳጥተው ከሚገዙት ሃይሎች አንዱ እሱ ነው።

ይህንን ተረድቶ ራሱን ለቻለ የአገር ኢኮኖሚ፣ለነጻ ፖለቲካና ሳይጉደፈ ባህል መታገል ጸረኢምፔሪያሊስት ያሰኛል፡፡ ማለት የኢምፔሪያሊስቶችን ማንኛውንም ቀጥተኛም ሆነ ተዘዋዋሪ ተጽእኖ የሚከላከሉ ሁሉ ጸረኢምፔሪያሊስት ናቸው፡፡ጸረኢምፔሪያሊስት የሆነው አቋማችን ሊያቋቁቸውና ቦታ ሊሰጣቸው ይገባል፡፡እነዚህ ብቻ ሳይሆን እንቅስቃሴያችን ኢምፔሪያሊዝምን የማይደግፉንና ስለኢምፔሪያሊዝም ለማወቅ የሚፈልጉን ሁሉ አብሮ ለማሰለፍ መጣጣር አለበት፡፡

እናጠቃል፡፡ጸረኢምፔሪያሊስትና ጸረባላባት አቋም ባሁኗ ኢትዮጵያችን ከተማሪውም ሆነ ከጠቅላላው ህብረተሰባችን ውስጥ ተበዝባዡንና ተቆርቋሪውን ሁሉ — ዘጠና በመቶውን ማለት ነው — ባንድነት ሊሰበስብና ሊያሰልፍ የሚችል ስፊ መሰረት ሊኖረው ይገባል፡፡የሰርቶአደሩን፣የንኡስከበርቴውን፣የብሄራዊ ከበርቴውን መደቦች ባንድ ላይ ሊያሰማራ ይችላል፡፡የላብአደሩን ማህበራት፣ብሄራዊ እንቅስቃሴዎችን፣የባህል፣የሃይማኖት፣የከፍለሀገር፣የወጣቶች፣የሴቶች፣ ... ድርጅቶችን ሁሉ ባንድነት ሊያሰልፍ ይችላል፡፡ባጭሩ ጸረባላባትና ጸረኢምፔሪያሊስት አቋምና ፖለቲካ የግንባር አቋምና ፖለቲካ ነው፡፡የፖለቲካ ፓርቲ አቋምና ፖለቲካ አይደለም፡፡ ይህን እውነት ከተቀበልን የተማሪ ማህበሮቻችንም ከተማሪው ውስጥ ዘጠና በመቶውን ባንድነት ለማሰለፍ መቻል አለባቸው ማለት ነው፡፡ሀቁ ቢታይ ግን ባሁኑ ጊዜ በንቅስቃሴያችን



— በተለይ በውጭ አገሩ — ውስጥ የሚሳተፈው ተማሪ ቁጥር ከዚህ በጣም የራቀ ነው፡፡የሚታሰብበትና በፍጥነት መሻሻል ያለበት ጉድለት ነው፡፡

እዚህ ላይ አንድ ነገር ማንሳቱ ጠቃሚ ይመስለናል፡፡ ይህ አቋም በመጀመሪያ ላይ ሲያዩት ቀላል ይመስላል፡፡ነገር ግን አይደለም፡፡አቋማችንን በድርጊት ላይ በምናውልበት ጊዜ ብዙ ችግሮች ሊገጥሙን ይችላሉ፡፡ጸረባላባታዊና ጸረኢምፔሪያሊስት ፖለቲካን በትክክል ከስራ ላይ ለማዋል መቻል፣ከዚሁ ፖለቲካ ክልል ውስጥና ውጭ የሆኑትን ጊዜያዊ ጥያቄዎች መርምሮ በትክክለኛው ቦታቸው ማስቀመጥ፣በማህበር ውስጥ የሚነሱትን አከራካሪ ነጥቦች እስከየት መሄድ እንዳለባቸው ማወቅ፣አንድነታችንን እየጠበቀ ጠቅላላውን ትግል ወደከፍተኛ ደረጃ ማድረስ ቀላል ነገር አይደለም፡፡በተለይ ከማህበራት አመራሮች ከፍ ያለ የፖለቲካ ንቃትን ይጠይቃሉ፡፡

ሊነሱ የሚችሉት ጥያቄዎች ብዙዎች ናቸው፡፡በተነሱ ቁጥር በቶሎ ይዘታቸውን ለመረዳትና ትክክለኛ መፍትሄያቸውን ለማግኘት ዝግጁ ሆኖ መጠባበቅ ያስፈልጋል፡፡መቼም ባንድ ማህበር ህይወት ውስጥ ሊደርሱ የሚችሉትን ጊዜያዊ ጥያቄዎች በቅድሚያ ዘርዝሮ ለማስቀመጥ አይቻልም፡፡በየእለቱ አዳዲስ ችግሮች ከፊታችን ተደቅነው ውሳኔን፣መፍትሄን፣እርምጃን ይጠይቃሉ፡፡ለነዚህም ችግሮች ጸረባላባትና ጸረኢምፔሪያሊስት አቋማችንን መለኪያ በማድረግ ትክክለኛ ቦታቸው

ን መስጠት ይኖርብናል፡፡ይህ ሁሉ ተግባር ከተማሪ ማህበሮ ቻችን አመራሮችና አባሎች ትልቅ አብዮታዊ ንቃትንና ትጋት ን ይጠይቃሉ፡፡የማህበር አመራሮችና አባሎች ባንድ በኩል ከንኡስከበርቴው ገልፍተኛነትና ችኩልነት፡በሌላው በኩል ደ ገኞ አጻጺስ አሳቦችንና አርምጃዎችን በመፍራት ወደኋላ ከ መጉተት መጠበቅ ይኖርባቸዋል፡፡መሰረታችን ጠብቆ የማህበሮ ቻችንን አንድነት ለማጠንከርና ወደፊት ለመገፋት የምንችለ ው በዚህ አኳኋን ነው፡፡

የአንድነታችን መሰረት ይጥበቅ

አንድነታችን ይጠንክር




1 "ትግሳችን" ልዩ ቱጥር፡ መስከረም 1963

2 MAO TSE-TUNG
Selected readings, Peking 1971, page 93

3 MAO TSE-TUNG
Speach at the chineese Communist Part's National Conference on Propaganda work, 1st pocket ed., 1957, page 26-27

4 SOMBART WERNER
Socialism and the scial movement in the 19th Century, tra. by A. P. Atterbury, page 110

5 LENIN
Coll. Works, Vol. 7, 1965, page 46

6 Ibid., page 69

የመፅሄት አዘጋጅ ቦርድ፥
P.O.BOX 3198
103 64 STOCKHOLM 3
SWEDEN

ዋጋው፣ 1.50 ብር